«‹እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።››

ኢሳ. ፶፫፥፭

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ


የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ቅዱስ ፓትርያርኩ የትንሣኤ በዓል የሞራል ትንሣኤ እንዲኖረን እንደሚያነሣሣ ገለጡ

ካሳሁን ለምለሙ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት

በየዓመቱ ታስቦ የሚውለው የትንሣኤ በዓል የሞራል ትንሣኤ እንዲኖረን የሚያነሣሣ ነው ሲሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ሚያዚያ ፲፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ገለጡ፡፡

እኛ ክርስቲያኖች በምድራዊ ሕይታችን ከግብረ ኀጢያት ርቀን በበጎ ሥራ አሸብርቀን፣ በፍቅርና በአንድነት፣ በስምምነትና በመቻቻል፣ በመተዛዘንና በመተሳሰብ በዕርቅና በሰላም እንድንኖር የሞራል ትንሣኤ እንደሚያስፈልገን ያስረዱት ቅዱስ ፓትርያርኩ "በመንፈሳዊ ሕይወታችን በኩል ደግሞ ከሞት በኋላ ያለውን ትንሣኤና የማያልቅ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዲኖረን ያስችለናል" ብለዋል፡፡


የክርስቶስ ትንሣኤ ጥላቻንና እርስ በርስ መጠፋፋትን ያስወገደ፣ሰላምን ያሰፈነና ዕርቅን ያረጋገጠ መሆኑን የተናገሩት ቅዱስ ፓትርያርኩ በመግለጫው "እኛም በዓለ ትንሣኤን ስናከብር የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መሆናችንን አውቀን እርሱ የሚወደውን ሥራ ብቻ በመሥራት ሊሆን ይገባል" ብለዋል፡፡

በትንሣኤ በዓል ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም መተባበር ክርስቲያናዊ ግዴታችን ሊሆን ይገባል ያሉት ቅዱስ ፓትርያርኩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በትንሣኤ በዓል ዕለት ተርበውና ተጠምተው፣ታርዘውና ተስፋ ቆርጠው እንዳይውሉ የሚያስፈልጋቸውን በማቅረብ በዓሉን አብረናቸው እንድንውል አሳስበዋል፡፡

የሰላምና የፍቅር፣የዕርቅና የይቅርታ ኃይሎች በመሆን ሀገራችንን ከፈተና ሕዝባችንን ከሰቆቃ እንታደግ በማለትም ለመላው ኢትዮጵያውያን አባታዊ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

# በዚህ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ግዴለሽነትና ቸልተኝነት ሊኖር እንደማይገባ ተገለጠ

ካሳሁን ለምለሙ



የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ የመጻሕፍት ርክክብ ሲያደርጉ

በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ግዴለሽነትና ቸልተኝነት ሊኖር እንደማይገባ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ከትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም የተበረከተላቸውን መጻሕፍት በተቀበሉበት ወቅት ገለጡ፡፡

"በነገሮች ሁሉ የምናሳየው ግዴለሽነትና ቸልተኝነት ስለማይጠቅመን ልናስብበት ይገባል" ያሉት ብፁዕነታቸው "በሚያወጡት ዐሥራት ቤተ ክርስቲያንን ይረዱ የነበሩ ምእመናን በወቅታዊ ችግር ምክንያት

በየአካባቢው አዝነውና ቆዝመው እያየን በቸገራቸው ወቅት መድረስ ያለመቻል በታሪክ ተጠያቂ ያደርገናል" ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አክለውም የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሕዝበ ክርስቲያን በሀብት መጎዳቱን አስረድተው "ከሀብታቸው መጎዳት በላይ ግን ምእመናንን የጎዳቸው አብያተ ክርስቲያናት በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከነቅርሶቻቸው መውደማቸው ነው" ብለዋል፡፡ እስካሁን ደረስ በሀገረ ስብከቱ ውድ ቅርሶችን የያዙ ጥንታዊና ታሪካዊ አንድ መቶ ዘጠኝ አብያተ ክርስቲያናት መውደማቸውንም ገልጠዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አያይዘውም "ከነቅርሶቻቸው ለወደሙ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት አብያተ ክርስቲያናት ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት የመጻሕፍት ድጋፍ ማድረጉ እንደ ቀላል ነገር የሚታይ አይደለም" ካሉ በኋላ "የምግብ ስጦታ ቢሆኑ ኖሮ ተመግበናቸው ቶሎ የሚያልቁ ሲሆኑ የመጻሕፍት ስጦታ መሆናቸው ግን ለዓመታት እየተመገብናቸው የሚቆዩ ምግበ ሕይወት ምግበ ነፍስ ናቸው" ብለዋል፡፡ ማተሚያ ድርጅቱ ላበረከተላቸው የመጻሕፍት ስጦታም በእግዚአብሔር ስም አመስግነዋል፡፡

በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ከጎደላት ነገር መካከል አንዱን ማሟላት መቻላችሁ ጥሩ ጅምርና የሚያኮራ ተግባር ነው ያሉት ብፁዕነታቸው እንደዚህ መረዳዳትና መደጋገፍ ብንችል ኑሮ ያለ ምንም ችግር የቤተ ክርስቲያናንን አገልግሎት በመላው ዓለም ማስፋት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

በዚህ ሰዓት ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት ለሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ያደረገው የመጀመሪያ ዙር የመጻሕፍት ድጋፍ በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ያሳሰቡት ብፁዕነታቸው "ቤተ ክርስቲያናችን ሁሉ ያላት የማትቸገር ብትሆንም የሀብት አጠቃቀማችን ጉድለት ያለበት በመሆኑ የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናትንና ምእመናንን በፍጥነት መታደግ እንቸገራለን" ብለዋል፡፡

በመጨረሻም በስጦታ የተበረከቱት መጻሕፍት በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙ ደቀ መዛሙርት የብዙ ጊዜ የአእምሮ ቀለብ እንደሚሆኑ ያስረዱት ብፁዕነታቸው "ከመስጠት በፊት ማሰብ ይቀድማልና በችግር ላይ ወድቀው ለከረሙ የሀገረ ስብከቱ ደቀ መዛሙረት በማሰብ የመጻሕፍት ድጋፍ ማድረጉ የሚበረታታ ተግባር ነው" ሲሉ ገልጠዋል፡፡

የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት መልአከ ሰላም ቀሲስ ሰሎሞን ቶልቻ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በችግር ላይ ለወደቀው የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ያበረከቱት መጠነኛ የመጻሕፍት ድጋፍ በብዙ እንዲባረኩ እንዳደረጋቸው ገልጠው ድጋፉን ያደርጉት የተቸገሩ ደቀ መዛሙርትን ለመርዳት ብቻ ሳይሆን ማተሚያ ቤቱ በረከት እንዲያገኝና የተሻለ ሥራ ለመሥራት እንዲያግዘው በማሰብ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ዋና ሥራ አስኪያጁ አክለውም ቤተ ክርስቲያንን፣ ምእመናንና አገልጋዮችን ማገዝ በደስታቸው ጊዜ ብቻ ሳይሆን በኃዘናቸው ጭምር ሊሆን እንደሚገባ ገልጠው "በማንኛውም አስቸጋሪ ጊዜ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከምእመናንና ከአገልጋዮች ጎን መቆም ሃይማኖታዊ ግዴታችን ልናደርግ ይገባል" ብለዋል

ሥራ አስኪያጁ አያይዘውም ለሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት መቶ አንድ ሽህ አምስት መቶ ብር የሚያወጡ የተለያዩ ሃይማኖታዊ መጻሕፍት ድጋፍ እንደተደረገ ተናግረው የተደረገው የመጻሕፍት ድጋፍ የመጀመሪያ ዙር በመሆኑ ለወደፊቱም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አክለውም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት አቅሙን እያጠናከረ ሲመጣ ለሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም አህጉረ ስብከት ተደራሽ እንደሚሆን አስረድተው "ከምናገኘው ትርፍ፣ ከጉለበታችንና ከሌላው ላይ ቀንሰን በልዩነት የአብነት ትምህርት ቤቶችን ማእከል አድረገን ድጋፍ የምናደርግም ይሆናል" ብለዋል፡፡

# የትላንት የቤተ ክርስቲያን ሰቆቃ ነገም እንዳይቀጥል የድርሻችንን እንወጣ

ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ ብዙ መከራና ስቃይን በጫንቃዋ ላይ ተሸክማ ትገኛለች። ከተለያዩ አቅጣጫዎች ያነጣጠረው ይኸው ዘርፈ ብዙ ዘመቻ እያሠለሰ አንደኛው ቁስል ሳይጠግ ሌላ ቁስልን እየጨመረ ምእመናን በስጋት ቤተ ክርስቲያን በፍርሃትና በመሸማቀቅ እንድትኖር እየዳረጋት ይገኛል፡ ፡ ከሰማያዊው አገልግሎት እያዘናጋ በዕለት ዕለት ሥራ እንድትጠመድ፤ ከመንፈሳዊ አግልግሎቷ ፊት እየቀደመ በምድራዊ አጀንዳ እንድትባዝን የሚደረገው ትንኮሳ ቀላል አይደለም። የውስጥ ሽኩቻው፣ ውጫዊው ተፅዕኖው ለቤተ ክርስቲያን እና በምእመናን ላይ የስጋት ደመና እንዲያንዣብብ ትልቅ ምክንያት ሆኗል።

ትላንት አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ ምእመናን ሲገደሉ፣ የቤተ መቅደስ አገልጋይ ካህናት ሲታረዱ፣ ዜጎች ሀብት ንብረት ካፈሩበት፤ አፈር ፈጭተው ካደጉበት እና ወልደው ከሳሙበት ፣ከኖሩበት ቀየአቸው እንዲፈናቀሉ፣ እንዲሰደዱ ተደርገዋል። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በመሆናቸው፣ ቤተ ክርስቲያንን በመርዳታቸው፣ ወጣቶችን ሰብስበው በማስተማራቸው በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በመሆናቸው ብቻ ብዙዎች የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዳጊ ሕፃናት፣ ሴቶችና ወንዶች ወቅት ተኮር ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል።

ሆኖም እንዲህ ዓይነቱን ገሀድ የወጣ ጥላቻና የጥፋት ዘመቻ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በቸልታ አላዩትም። ይልቁንም የርስ በርስ ግጭት እንዳይመጣ፤ የባሰ እልቂት እንዳይከሰት በተለይም የሀገር ሰላም እንዲጠበቅ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀውን ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል። እየተካሄዱ ያሉትን ኦርቶዶክስ ጠል ዘመቻዎች በሆደ ሰፊነትና በአርቆ አስተዋይነት ለማለፍ ሞክረዋል። ጉዳት የደረሰባቸውን ምእመናን በማጽናናት፣ በማረጋጋት እና አማራጭ መፍትሄን በመስጠት ሰላም እንዲመጣ ብዙ ጥረዋል። ይህ ሆኖ ሳለ የሔዱበትን የጥበብ መንገድ እንደ ሞኝነትና እንደ ፍርሃት በመቁጠር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የማሳደድና የማጥቃት ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠሉ የዐደባባይ ምሥጢር ሆኗል።

በትላንት ብቻ ያላበቃው ቤተ ክርስቲያንን የማሳደድ ዘመቻ ዛሬም እንደ ዐዲስ መቀጠሉ ነገ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያነጣጠረ ሌላ ጥቃት ስለመኖሩ ነቢይ መሆን አያስፈልግም። ለዚህ ማሳያው በጥምቀት በዓል ላይ ታድመው የነበሩ የወይ ብላ ማርያም አካባቢ ምእመናን ላይ የደረሰው ጥቃትና ሞት የምእመናን ቁስል ሳይጠግንና እንባቸው ሳይደርቅ ዛሬም በአቃቂ ቃሊቲ በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ጠብ አጫሪነት በተፈጠረው ግርግር የተገደለው ኦርቶዶክሳዊ ወጣት አንዱ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባቶች መንግሥት እንዲህ ዓይነቱን ጠብ አጫሪነት የሚያነሣሱ ድርጊቶች እንዲቆሙ መጠየቁና የገዳዮች ለፍርድ እንዲቀርቡ መጠየቁ ተገቢም ወቅታዊም ነው። ሆኖም የተጠናከረ ጥያቄና ለጥያቄው ዘላቂ መልስና መፍትሄ አብሮ መፈለግም ከቤተ ክርስቲያንም ከመንግሥትም ይጠበቃል። ለፈሰሰው የምእመናን ደም ተጠያቂ የሆነ እና ኃላፊነት የሚወስድ አካል የምእመናን እንባ በሚታበስበት እና ልባቸው በሚያርፍበት መልኩ ለፍርድ እንዲቀርብ ጠንክሮ መሥራት አስፈላጊ ነው።

ዛሬም ባላቆመውና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ህልውና በሚፈታተነው እኩይ ተግባር ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ግለሰቦች እና ተቋማት ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው መቅረቱ፣ ነገም ስጋት ሆኖ መቀጠሉ ወደ ተስፋ መቁረጥ እንዳያመራ ያሰጋል ያስፈራልም። ነገሮች ወደ ጥፋት ከማምራታቸው፣ ምእመናን ለሞት እና ለእንግልት ከመዳረጋቸው በፊት ስጋት የሆኑ ጉዳዮች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አስፈላጊ ነው። በየጊዜው ምክንያት እየተፈለገላቸው የሚከሰቱና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መብት የሚጋፉ ድርጊቶችን በማውገዝ፣ በማጋለጥ፣ ከመንግሥት አካላት ጋር ጠንከር ያለ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው።

የሚችን ብዛት እየቆጠሩ ከመብከንከን፣ ከንፈር ከመምጠጥ እና የአንድ ሰሞን ብቻ አጀንዳ አድርጎ ከመንቀሳቀስ ለቤተ ክርስቲያን እና ለከበረው አገልግሎቷ እንቅፋት የሆኑ

ነገሮችን፣ ግለሰቦችን እና ተቋማትን ለይቶ አውቆ ለቤተ ክርስቲያን እንቅፋት የሆነውን ሰንኮፍ ከሥሩ ነቅሎ መጣል፤ ምንጩን ማድረቅ ከእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ልጅ የሚጠበቅ ተግባር ነው። በየትኛውም ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን፤ ዙሪያ ገቧን ማጤን እና መጠበቅ፤ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን ለከፋ አደጋ እያጋለጧት ያሉትን እኩይ ተግባሮች ፊት ለፊት በመጋፈጥ አለኝታና ብርታት መሆን ይገባል።

የተጎዱትን መሰብሰብ፣ የኔ ብሎ መደገፍ፣ ጉዳዩን ጥግ ድረስ ሄዶ መከታተል ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ልብ ሊለው የሚገባ ተግባር ነው። ይህንን ለማድረግ ኦርቶዶክሳዊ ቁመና አስፈላጊ ነው። ይህንን ለማድረግ ኦርቶዶክሳዊ መግባባት ቸል የማይባል ነው። ይህንን ለማድረግ መዋቅሩን የጠበቀ ተዋረድነት ያለው ተግባቦት ጊዜው የሚጠይቀው ዐቢይ ጉዳይ ነው። አንድነትን፣ ኅብረትን የተማርነው ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነውና ኅብረታችን የጠበቀ ሊሆን ተገቢ ነው። የአንድ ሰው ስደት ሁሉን ኦርቶዶክሳዊ ካላሳዘነ፤ የአንድ ኦርቶዶክሳዊ ሞት ሁሉን የቤተ ክርስቲያን ልጅ ካላስቆጨ ነገ የእያንዳንዱን በር የማያንኳኳበት ምክንያት አለመኖሩን ሁሉም ልብ ሊል ይገባል።

የርስ በርስ ግንኙነትን ማጠንከር፣ ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ፣ ስለተጎዱት፣ ስለሞቱት መጮኽ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ብቻ ሊሆን አይገባም። ሁሉም ባለበት እንደየድርሻውና እንደልጅነቱ፣ በተገኘበት፣ በሚሠራበት፣ በተቀመጠበት ወንበር፣ በተሰጠው ሥልጣን የቤተ ክርስቲያን ሰቆቃ የሚቀንስበትን መንገድ መፈለግ ክርስቲያናዊ ግዴታው፣ የእናት ቤተ ክርስቲያንም ጥሪ ነው። የምዕራቡ ለሰሜኑ ክርስቲያን፤ የደቡቡ ለምሥራቁ ክርስቲያን እኩል ሊጮኽለት፤ እኩል ሊደርስለት ይገባል። ከመግለጫዎች፣ ከቴሌግራም መልእክቶችና ከዘጋቢ ፊልሞች በተጨማሪ መሬት ላይ የወረደ፣ የርስ በርስ መስተጋብር፣ የጠበቀ ግንኙነት በተዋረድ እና በጎንዮሽ መመሥረት ዘመኑ የሚጠይቀው ታላቅ ተግባር ነውና ለዚህ ልንተጋ ይገባል።

ጊዜያዊ እሳትን ማጥፋት ብቻውን ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ምእመናኑን አይጠቅምም። እስከዛሬ የሄድንባቸው መንገዶች ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ እየጎዱ፣ ምእመኑን ይበልጥ ተስፋ እያስቆረጡ የመጡ ተደጋጋሚ ጥቃቶች ናቸውና በውል ተገንዝቦ መሥራቱ ነገን ከስጋት ነፃ ያደርገናል። ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣትን የኖላዊነት አገልግሎት በሥርዓት እንዳትከውን እዚህም እዚያም የሚደረጉትን ትንኮሳዎች ለማስቆም ተናቦ መሥራት፤ ተግባብቶ መሄድ አስፈላጊ ነው። ይልቁንም በእያንዳንዱ ቀንና ቦታ የሚደረጉትን ኦርቶዶክስ ጠል እንቅስቃሴዎች በንቃት መከታተልና መጠበቅ ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ግዴታ ሊሆን ይገባል።

# ሞዐ ተዋሕዶ የቤተ ክርስቲያንን ጥያቄዎች ለማስመለስ እየሠራሁ ነው አለ

ክፍል አንድ

በሻምበል ጥላሁን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ መሠረትነት ላይ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በፈተና ውስጥ እያለፈች አሁን ካለንበት ዘመን እንደደረሰች ሁሉም የሚስማሙበት ሐቅ ነው፡፡ የሀገር ባለውለታ የሆነችው ጥንታዊቷ፣ ታሪካዊቷና ብሔራዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የሥርዓተ መንግሥት ለውጥ በመጣ ቊጥር፣ ከለውጡ ጋራ ተያይዘው በኅብረተሰቡ ላይ የሚከሠቱ ችግሮች ሰለባ እየሆነች እንደሆነም ክስተቶቹ ሕያው ምስክሮች ናቸው፡፡ የሥርዓተ መንግሥት ለውጡ በመጣ ቊጥር የሚደርስባት ችግሮች የበለጠ እንዳይባባሱና የከፋ አደጋ እንዳያመጡ በማሰብ ችግሮቹን በትዕግስት ብታልፍም፣ ለውጡን ተከትሎ ወይም ተገን አድርጎ የሚነሣ ፀረ ክርስትና ቡድን በሚወስደው ኢ-ሰብአዊ ርምጃ ምክንያት የምእመናን በክርስትናቸው ምክንያት መገደል፤ መሰደድ እና ሀብት ንብረታቸው መዘረፍ የቤተ ክርስቲያን መቃጠል፤ ከመቼውም በላይ የቤተ ክርስቲያንን ልዕልና የሚጋፋ እየሆነ መጥቷል፡፡ የደረሰባትን ጉዳትና ችግር ሁሉ በትዕግሥት፣ በአርምሞና በጽሞና ማሳለፍ ከጀመረችም እነሆ ግማሽ ምዕት ዓመትን አሳልፋለች፡፡

በተለይም ከ፲፱፻፶ዎቹ ጀምሮ ቅርጹን ቀይሮ የቀጠለው ሁለንተናዊ የአስተሳሰብ ውጊያ በጊዜ ሂደት መዋቅራዊ ወደ መሆን እያደገ ሄዶ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በእነዚህ በርካታ ዓመታት ውስጥ ሲካሄድ የቆየውን ጥቃት ማሳያ የሆኑ በርካታ ክሥተቶችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ የሩቁን ለታሪክ እንለፈውና በቅርቡ የተደረገውን ስናስታውሰው፣ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በአርሲ ሀገረ ስብከት በኮፈሌ ወረዳ ውስጥ የምትገኘው የአይሻ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ በወቅቱ በተፈጠረው ምርጫ ግርግር ምክንያት ፀረ ክርስትና አቋም ባለው ቡድን ስትቃጠልና አገልጋዮቿ ካህናት በቤተ መቅደስ ውስጥ ታርደውባታል፡፡ እንደገናም በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በጂማ ሀገረ ስብከት የበሽሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ጥቅምት ፳ ቀን በዕለተ በዓሉ በፀረ ክርስትና ኃይሎች ሲቃጠልና አገልጋዮቿ ካህናትና ተከታዮቿ ምእመናንም በቤተ መቅደሱ ውስጥ እንደ በግ ሲታረዱ አሁንም ለኅብረተሰቡ የከፋ እልቂት እንዳይደርስ በማሰብ በብዙኃን ተከታዮቿ ዘንድ እየታማች ጉዳቷን ጉዳት አድርጋ ድምፅዋን ሳታሰማ በትዕግሥት ማሳለፏ ይታወሳል፡፡

በተለይም ብዙ ተስፋ የተደረገበትን የአሁኑን ለውጥ ተከትሎ በ፳፻፲ ዓ.ም መገባደጃ ላይ፣ አገር የሆነችውን በሁለንተናዊ ጠቀሜታዋና ትሩፋቷ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ የሆነችውን አንጋፋዋን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው ነጥሎ ለመምታትና የተከታዮቿ ምእመናንን አሻራ ከገጸ ምድር ለማጥፋት ወይም አሳምኖ የራሱ ተከታዮች ለማድረግ፣ የረዥም ጊዜ ዕቅድ ባለው ፀረ ክርስትና ቡድን በተፈጸመ ጥቃት፣ በሱማሌ ክልል ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያን በሙሉ መውድሟቸው፤ ሀብታቸው፣ ንብረታቸውና ቅርሶቻቸውም መዘረፋቸው፤ አገልጋዮቿ ካህናትም እንደ ካህኑ ዘካርያስ በየቤተ መቅደሳቸው ውስጥ መታረዳቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብቻ በማነጣጠር መዋቅራዊ በሚመስል ሁኔታ ከ፳፻፲ ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ የተፈጸመው ይህ ዐይነቱ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ጥቃት ከትዕግሥት በላይ ቢሆንም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሀገር እንደ መሆኗ መጠን፣ አሁንም በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በሕዝብ ላይ የበለጠ ጉዳት እንዳይደርስ በማሰብ ብዙ መጎዳቷንና መጠቃቷን ለመንግሥትና ለሕዝብ ይፋ ያደረገችው ከብዙ ጉዳትና ትዕግሥት በኋላ መሆኑም ይታወቃል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ትዕግሥት በኋላ ጥቃቷን በዐደባባይ ወጥታ መንግሥት እንዲያስቆምላት ብትጠይቅም አሁንም

በሀገሪቱ በርካታ ስፍራዎች የአምልኮ ቦታዎች እየተነጠቁ ነው፡፡ ሕዝበ ክርስቲያኑም የዐደባባይ አምልኮ ሥርዓቱን በአግባቡ እንዳይፈጽም በጥቂት ባለ ሥልጣናት ትእዛዝና በጥቂት ሕግ አስከባሪዎች የሚደርስው ውክቢያ ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰ የተለያዩ ኦርቶዶክስ ተኮር ጥቃቶችም ሲፈጸሙ እየታየ እየተሰማ ነው፡፡ እነዚህንም ጥቃቶች በተደራጀና በሰላማዊ እንቅስቃሴ ለመከላከል፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን መብት ለማስጠበቅ፤ ማኅበራት፣የማኅበራት ኅብረቶችና ጥምረቶች በመመሥረት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ማድረግ መጀመራቸው ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ ማኅበራቱም ሆኑ ጥምረቶቹ በሚከሠቱ ደራሽ ምክንያቶች ከሚያስሟቸው ብሶቶችና የአቋም መግለጫዎች በዘለለ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን መዋቅራዊ ጥቃት ማስቆም አልቻሉም፡፡ ይሁንና ከሰሞኑ ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የገጠማትን ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ታሳቢ ያደረገ የኦርቶዶክሳውያን ጥያቄዎችን ለማስመለስ የሚሠራ ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› የተባለ ግብረ ኃይል ተቋቁሟል፡፡ በዚህ የዜና ትንታኔ ሞዐ ተዋሕዶ ማን ነው? ስያሜውስ ምን ማለት ነው? የቤተክርስቲያንን ጥያቄዎች ከማስመለስ አንጻር ምን እየሠራ ነው? በግብረ ኃይሉ ላይ የምእመናን ተስፋና ሥጋት ምንድንናቸው? በሚሉ ነጥቦች ላይ የምእመናንን አስተያየት አካተን ተከታታይ ጽሑፍ እናቀርባለን፡፡

መምህር ፋንታሁን ዋቄ ስለ ሞዐ ተዋሕዶ ስያሜ በግብረ ኃይሉና በሌሎች መንፈሳዊ የማኅበራዊ ትሥሥር ገጾች ላይ ላይ እንደተናገሩት፤ ስያሜውን ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› ያልንበት ምክንያት ተዋሕዶ ማለት የአምላክ ሰው መሆን፤ የሰው አምላክ መሆን፤ ያለመጠፋፋት፤ የሰውን ልጅ ሞት ለማዳን ሰው የሆነውን አምላክ የምንገልጽበት ነው በማለት ያስረዳሉ መምህሩ፡፡ ይህ ምሥጢር ግን ይላሉ ምምህር ፋንታሁን፤በዚያ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፤ በፍጹም አሸናፊ የሆነ አምላክ ሰው የማያሸንፈውን ሞት ያሸነፈበትን መንገድ የሚገልጽም ነውና ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› ብለዋል፡፡ ‹‹ሞዐ›› ማለትም በግእዝ ቋንቋ አሸነፈ፤ ድል አደረገ ማለት ሲሆን፤ ከዚህ ሥርወ ቃል የሚገኘው ‹‹ሞዕ›› የሚለውም ተዋሕዶ ከሚለው ቃል ጋር ሲናበብ ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› የሚል ጥምር ያስገኝልናል ሲሉም ስለስያሜው ያብራራሉ መምህሩ፡፡ ትርጉሙም የተዋሕዶ አሸናፊነት ማለት ነው ሲሉም ያክላሉ፡፡ እኛም ስሙን ሞዐን ከተዋሕዶ ያጣመርንበት ምክንያት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አሸናፊ ናት ለማለት ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም አሸናፊው አምላክ ለሰው ልጆችም ድኅነት የሰጣት ብቸኛዋ መንገድ ነችና፡፡ የአሸናፊ ልጆች ደግሞ እንሠራለን ብለው ከተነሡ ያሸንፋሉ ብለን ነው የምናምነው የሚሉት መምህሩ፣ አሸናፊው አምላክ ራስ የሆነላትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለማለትም ነው ስያሜውን ያወጣነው በማላትም ያብራራሉ፡፡

ስያሜውን በዚህ መልክ የገለጹት መምህር ፋንታሁን ግብረ ኃይሉ ማን ነው ለምንስ ተመሠረተ? የሚለውን ሲገልጹም፤ ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላት መንፈሳዊም ሆነ ባህላዊ መንግሥታዊ መዋቅር የኖሩባት ሀገር ናት፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ባህላዊና መንፈሳዊ መዋቅራት ካለፉት ኀምሳ ዓመታት ወዲህ መንግሥት በሚባለው መዋቅር በመደፈር፣ ባለመደመጥ አደጋ ላይ መውደቅ ጀመረ በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ሠላሳና ዓርባ ዓመታት እጅግ በከበደ ሁኔታ ደግሞ ባለፉት አራት ዓመታት ቅድስት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የሚደርሰው ጥቃት፤ ተጠያቂውና ተበዳዩን በሚመለከት ምላሽ አላገኘም ይላሉ መምህሩ፤ በደሎቹን በተለመዱት መዋቅሮች መልስ ለማግኘትም የተለያዩ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅበራትና ተቋማት በጉዳዩ ላይ መልስ ለማግኘት ተነጋግረውም ተደራድረውም ነበረ ሲሉ ያስታውሳሉ መምህር ፋንታሁን፡፡ ይሁን እንጂ ችግሮቹ ተባብሰው ቀጠሉ እንጂ መፍትሔ አላመጡም ሲሉም ያስረዳሉ፡፡ ጥቃቱም ሥርዓታዊ፣ርእዮተ ዓለማዊና መዋቅራዊ ግብ ያስቀመጠ መሆኑ ግልጽ ወጥቷል ብለው ይሞግታሉ፤መምህሩ አያይዘውም የዜጎችን ደኅንነት መጠበቅ የሚገባው መንግሥት በተለይም ለኦርቶዶክሳዊው ማኅበረሰብ ጥበቃ ካለማድረጉ ባሻገር ኦርቶዶክሳዊ ማኅበረሰብ ሲበደል አይካስም፣ ታቅዶበትም ይሁን ድንገት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በተከሠቱ ችግሮች ኦርቶዶክስ ቢፈናቀልም መልሶ አያቋቁምም፤ አጥፊዎችንም በሕግ አይጠይቅም፡፡ በጣም የሚያስደነግጠው ነገር ጉዳዩ ትኩረት እንዳይሰጠው የመንግሥት ሚዲያዎችም እነዚህን ጥቃቶች ለመሠወር

ይሞክራሉ፤ ሚዲያዎቹም ብቻ ሳይሆኑ ሚዲያዎቹን የሚመሩ ባለ ሥልጣናት ጭምር በጥቃቶቹ ጊዜ ጉዳዩ ትኩረት እንዳያገኝ ለሚዲያው ሌላ አጀንዳ ሰጥተው ጉዳዩን ሲያልፉት እንደሚታይም ይገልጻሉ መምህር ፋንታሁን።

‹‹ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችም ሆኑ ዲፕሎማቶች ኦርቶዶክሳውያን ሲጠቁ ፈጽሞ አይናገሩም›› የሚሉት መምህር ፋንታሁን ለዚህ ማሳያ የሻሸመኔውን የኦርቶዶክሳውያን ጭፍጨፋ በምሳሌነት ያነሣሉ። ይህን መዋቅራዊና የተቀናጀ ጥቃት ስናይ አሁን ባለው የቤተ ክርስቲያን መዋቅርም ሆነ የማኅበራት የአገልጋዮች ስብስብ የሚያሰሙት ጩኸት አልሰማ ስላለ ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› የሚለው ግብረ ኃይል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኗል የሚሉት መምህር ፋንታሁን፤ ግብረ ኃይሉ ለምን አስፈለገ ለሚለው ጥያቄም "ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት ሥርዓታዊ፣ መዋቅራዊና ርእዮተ ዓለማዊ ጉዳይ መሆኑን በደንብ አጉልቶ በማሳየት ሕዝቡ ራሱን ከጥፋት እንዲከላከልበት መንግሥትም ምላሽ እንዲሰጥበት ግፊት ለማድረግና ለማስተባበር ግብረ ኃይሉ ተቋቁሟል ›› ሲሉ ይናገራሉ።

ወጣት ጴጥሮስ ጸጋዬ ደግሞ የአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም አጥቢያ ቤተክርስቲያን የፈለገ ኤማሁስ መንፈሳዊ ማኅበር አባል ነው። ሁለቱ አስተያየት ሰጪዎች ስለ ሞዐ ተዋሕዶ ግብረ ኃይሉ ምስረታ ተስፋና ስጋት አላቸው።

ወጣት ጴጥሮስ ጸጋዬ የሞዐ ተዋሕዶ ግብረ ኃይል መመሥረት ቢያስደስተውም ከዚህ በፊት እንደተመሠረቱት መሰል መንፈሳዊ ማኅበራትም ሆነ ግብረ ኃይሎች ሞዐ ተዋሕዶ ታይቶ እንዳይከስ ስጋት እንዳለው ይናገራል።

ቤተ ክርስቲያን አሁን ሀገር አቀፍም ሆነ አጥቢያ አቀፍ የሆኑ እልፍ አእላፍ ማኅበራት አሏት የሚለው ጴጥሮስ፤ ማኅበራቱ ይነስም ይብዛ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስፋፋትና መጠናከር የራሳቸው አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም ተቀናጅተውና ተናበው ባለመሥራታቸው ቤተ ክርስቲያንን ከጥቃት ከመከላከል አንጻር ድርሻቸው አነስተኛ ነው ይላል፤ አያይዞም ሞዐ ተዋሕዶም ከነዚህ ማኅበራት በምን ይለያል? ሲል ይጠይቃል።

የሞዐ ተዋሕዶ ግብረ ኃይል አባል የሆኑት ዲያቆን ዮሴፍ ከተማ ከወጣት ጴጥሮስ የተለየ አቋም አላቸው። ዲያቆን ዮሴፍ እንደሚሉት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ምእመናን አሏት ተብሎ ለምትገመተው ቤተ ክርስቲያን፤ በሀገር ውስጥ፣ በአፍሪካና በተለያዩ ዓለም ሀገራት ሀገረ ስብከት ከፍታ ለምትንቀሳቀስ ቤተ ክርስቲያን አሁን ያሉት ማኅበራት በዝተዋል ሊባሉ አይችሉም ይላሉ፤ ቤተክርስቲያን እንደአላት ሃምሳና ስድሳ ሚሊዮን ተከታይ ብዙ ማኅበራት አሉ ብዬ አልገምትም ሲሉ የጴጥሮስን ሐሳብ የሚሞግቱት ዲያቆኑ ይልቅስ መጠየቅ ያለበት ማኅበራቱ ምንድን ነው የሠሩት? እንዴትስ ነው የተዋቀሩት? በምን ዘርፍ ላይ ነው ተሰማርተው ያሉት? ውጤታማነታቸውስ እንዴት ነው? ቢባል ጥያቄው ውኃ ያነሳል ይላሉ። ስለሆነም ዓለም አቀፍ ለሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አሁን የምናያቸው ማኅበራት በዝተዋል የሚለው ሙግት አያስኬድም ይላሉ ዲያቆን ዮሴፍ።

ስለ ሞዐ ተዋሕዶ ግብረ ኃይል ከሌሎች ማኅበራት ወይም መንፈሳዊያን ስብስቦች በምን ይለያል የሚለውንም ጥያቄ ዲያቆን ዮሴፍ ሲያስረዱ "ሞዐ ተዋሕዶ ማኅበር አይደለም ይላሉ፤ ሞዐ ተዋሕዶ እስከ አሁን የተቋቋሙት ማኅበራት፤ መደበኛ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን ጭምር በተለያዩ መንገድና በተለያዩ ጊዜያቶች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች አሉ፤ እንዚህን ጥያቄዎች እንዲያነሷቸው ያስገደዷቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሱ መከራዎች ናቸው። ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ማኅበራትም ሆኑ መንፈሳዊያን ስብስቦች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ሁሉ ሞዐ ተዋሕዶ አሰባስቦ እና በሰባት ክፍል ለይቶና ጥያቄዎቹን አደራጅቶ መልስ ለማሰጠት የተቋቋመ ግብረኀይል ነው" ይላሉ። በቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው ያሉ ማኅበራት እስከአሁን የሚያነሧቸውን፣ ጥያቄዎችን ሞዐ ተዋሕዶ በተደራጀ፣ በተጠናና በተሰባሰበ መልኩ ይዞ ወደ ፊት የወጣ ንቅናቄ ነውም በማለት አስተያየታቸውን ያክላሉ ዲያቆን ዮሴፍ።

# ከስደት መልስ በአርምሞ ያረፈች ነፍስ

በካሳሁን ለምለሙ


ክፍል አንድ

በጸሎት፣በሰላምና አንድነትን በመስበክ የሚታወቁ ታላቅ ታጋራሚ አባት እንደነበሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ ያሉ አበው ሊቃነ ጳጳሳትና የአኃት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ይናገራሉ። ትውልዱ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር እንዲመልስ ተግተው ያስተምሩና ይመክሩ ነበር። ለትውልዱ የነበራቸው ቀና አመለካከት የሚጀምረው ተማሪ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን ለትውልዱ ምሳሌ ለመሆንና ትውልዱ ከእግዚአብሔር እንዳይርቅ በፈተና ውስጥ ሆነው በርካታ አገልግሎቶችን ፈጽመዋል።

ለምድራችን በረከት ያመጡ ትምህርቶችን ያስተምሩ ስለነበረ የዚህ ዘመን ትውልድም ከእርሳቸው የአገልግሎት ሕይወት ብዙ ተምሯል ተብሎ ይታመናል። ፍጹም የሆነ የብሕትውና ሕይወትን ሲመሩ የነበሩ ደግና ለትውልዱ አዛኝ እንደነበሩ ምስክርነት የሚሰጡ አባቶች በርካታ ሲሆኑ ለአመኑበት ነገር ሁሉ ቆራጥና ጠንካራ እንዲሁም ችግሮችን በቀላሉ የመፍታት መንፈሳዊ ብቃት የነበራቸው መሆናቸውንም አጽንተው ይናገራሉ። ከመከፋፈል ይልቅ የሀገርንና የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ሰላም አጥብቀው የሚፈልጉ እውነተኛ አባት እንደነበሩና ዝምታቸው እንኳን የተጣላ አስታራቂ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል።

በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘመናቸው ሁሉ እወነተኛ መሪና አገልጋይ ነበሩ፤ ራሳቸው በከፋ ችግር ውስጥ ሆነው እንኳን ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ይበልጥ ሠርተዋል፤ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና ቤተ ክርስቲያን በውጭው ዓለም እንድትስፋፋ ሐዋርያዊ ተልኳቸውን በብቃት ሲወጡ የቆዩ ቅዱስ አባት ነበሩ። ቤተ ክርስቲያናችን አለኝ ከምትላቸው የሚወደዱና የሚከበሩ ሊቃውንት መካከል አንዱ ሲሆኑ ክፉና ደግ ሳለመናገር በዝምታ የቆዩና ዓለምን የናቁ እውነተኛ ታጋራሚ አባት ነበሩ። የበላዮቻቸውን አክባሪ፣ የበታቾቻቸውን መካሪ፣ በአገልግሎት ታታሪ፣ መንፈሳዊ አባትነታቸውና ትሑት ሰብእናቸው አርአያነት ያለው ቁጥብ አባት ነበሩ።

"እርሳቸውን የመሰለ የጸሎት፣ የበረከትና የአርምሞ ቅዱስ አባት ከዚህ ዓለም ድካም ማረፋቸው የሚያሳዝንና ብዙ ነገር የሚያጎድል ሲሆን በሕይወት ኖረው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ቢቆዩ ደግሞ ጸሎታቸውና በረከታቸው ይጠብቀን ነበር" ይላሉ አባቶች። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በሥጋ ቢለዩን ከምስጋና የበለጠ ወደ ምስጋና ስፍራ በመሄዳቸው ልናዝንና ልንተክዝ አይገባንም። እርሳቸው በዓለም በቆዩበት ጊዜ ሁሉ ትጉህ፣ ቆፍጣናና የውሳኔ ሰው ከመሆናቸው የተነሣ ለቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሉዓላዊነት አብዝተው የሚጨነቁና መስለው ሳይሆን ሆነው የኖሩ አባት ነበሩ። ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት የጸሎትና የበረከት አባት የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የዛሬ የቤተ አብርሃም እንግዳችን ናቸው። ቅዱስነታቸው የካቲት ፳፭ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም ከዚህ ዓለም ድካም ዐርፈው መጋቢት ፬ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥርዓተ ቀብራቸው መፈጸሙ ይታወሳል። ስለሆነም የቅዱስነታቸውን የልደት፣ የትምህርት፣ የሀገር ውስጥና የስደት የአገልግሎት ጊዜያቸውን በአጭሩ እናስቃኛችኋለን። መልካም ንባብ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

## ፩. ልደትና መንፈሳዊ ትምህርት

የቅድመ ጵጵስና መጠሪያቸው አባ ዘሊባኖስ ፈንታ በመባል ይታወቁ የነበሩት በአሁኑ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በቀድሞው አጠራር

በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በአንዳቤት ወረዳ ልዩ ስሙ አረጊት ኪዳነ ምሕረት ደብር ሰበካ ልዩ ስሙ ማር ምድር አካባቢ ከአባታቸው ከብላታ ፈንታ ተሰማና ከእናታቸው ከወይዘሮ ለምለም ገሠሠ በ፲፱፻፴ ዓ.ም ተወለዱ፡፡

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢው ከሚገኙት መሪጌታ ላቀው ንባብና ዳዊት ከተማሩ በኋላ በአጭቃን ኪዳነ ምሕረት ደብር ምዕራፍና ጾመ ድጓ ተምረዋል፡፡ ከዚያም ትምህርታቸውን የበለጠ ለመማር ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ሂደው ጕንጂ ቴዎድሮስ ገዳም ከመሪጌታ ወርቁ ዘንድ ሁለት ዓመት ቅኔ ከተማሩ በኋላ ዳግመኛ ወደ ዋሸራ መንክር ኃይላ ቅድስት ማርያም በመሄድ ስመ ጥር ከነበሩት ከታላቁ ሊቅ ከመሪጌታ ማዕበል ፈንቴ ደግሞ ሁለት ዓመት ተምረው በአጠቃላይ አራት ዓመታትን በመማር የቅኔ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡ ከዚያም ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው በደብረ ታቦር አውራጃ ልዩ ስሙ አጋጥ ጽዮን ደብር ከመሪጌታ ሙጬ ላቀ ዘንድ የምዕራፍ፣ የድጓና የጾመ ድጓ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡

ቅዱስነታቸው ከነበራቸው ከፍተኛ የትምህርት ፍላጐት የተነሣ ወደ አቋቋም ቤት በመግባት መነጕዘር ኢየሱስ በሚባለው ደብር ከመሪጌታ ሚናስ ለአራት ዓመታት ያህል የአቋቋም ትምህርት ተምረዋል፡፡ በመቀጠልም ቁት አቡነ አረጋዊ ደብር ከመሪጌታ ውብአገኝ ዘንድ ዝማሬ መዋሥዕት ተምረዋል፡፡ ከዚያም ከመጀመሪያው መምህራቸው መሪጌታ ሙጬ ላቀ ዘንድ እንደ ገና የድጓ ትምህርታቸውን በመከለስ ጽፈውና አመልክተው ከጨረሱ በኋላ፤ በቀድሞ አጠራር በጋይንት አውራጃ በታች ጋይንት ወረዳ ወደምትገኘው ቅድስት ቤተልሔም የድጓ ትምህርት ማስመስከሪያ በመሄድ ለአራት ዓመታት ያህል ቆይተው የድጓ ትምህርታቸውን በሚገባ በማጠናቀቅ አስመስክረው በመምህርነት ተመርቀዋል፡፡ ከዚያም ቅዱስነታቸው ተጨማሪ ትምህርት ለመማር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በቅዳሴና በማኅሌት አገልግሎት ተመድበው እያገለገሉ ትርጓሜ ሐዲሳትንና አቡሻኽርን ተምረዋል፡፡ ዘመናዊ (የአስኳላ) ትምህርታቸውንም በቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ተከታትለዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ለመምህራን የተዘጋጀውን የስብከት ዘዴ ትምህርት ለሁለት ዓመታት ተምረው ተመርቀዋል፡፡

## ፪. ክህነትና መንፈሳዊ አገልግሎት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የጎንደር ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል ዘንድ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም መዓርገ ዲቁና ተቀብለዋል፡፡ ቅዱስነታቸው ሥርዓተ ምንኵስናን ከመምህርነት ጋር አጣምሮ ለመያዝ ያላቸው መንፈሳዊ ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን በሙሉ አቅምና ጊዜ ለማገልገል የምንኵስና ሕይወት የበለጠ ተመራጭ መሆኑን ስለተረዱ በጣና ደሴቶች ካሉት ጥንታዊ ገዳማት መካከል አንዱ በሆነው በምኔተ አቡነ ኂሩተ አምላክ ዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ከመምህር ኃይለ ማርያም ዘንድ በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም መዓርገ ምንኵስናን፣ ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ደግሞ የቅስና መዓርግ ተቀብለዋል፡፡

ቅዱስነታቸው ከነበራቸው ጠንካራ መንፈሳዊ ሕይወት የተነሣ በባሕር ዳር አውራጃ ልዩ ስሙ ጋሾላ አቡነ ተጠምቀ መድኅን ወደሚባለው አንድነት ገዳም ገብተው የገዳሙን ሥርዓት አጥንተው ለገዳማውያን በመታዘዝ በተግባረ እድ፣ በትምህርት፣ በጸሎተ ማኅበር፣ ለእንግዶች የሚሆን ማረፊያ ቤት በመሥራትና አቅመ ደካሞችን በመርዳት ለሁለት ዓመታት ያህል በቅንነት አገልግለዋል፡፡

መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በዋናነት የጀመሩት በማስተማር ሲሆን፤ የድጓ ትምህርታቸውን ካስመሰከሩ በኋላ ወደ ተወለዱበት ገዳም አረጊት ኪዳነ ምሕረት ሂደው ለሰባት ዓመታት ያህል ድጓ አስተምረዋል፡፡ በተጨማሪም ወደ አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በመምጣት በቅዳሴና በማኅሌት ሰፊ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነውም አገልግለዋል፡፡ በአስተዳዳሪነት ዘመናቸው ለቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች መኖሪያ ቤት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችም የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከነሙሉ መገልገያው አሠርተዋል፡፡

ተጀምሮ የነበረውን የቤተ ክርስቲያኑን ሕንጻም እንዲጠናቀቅና በአካባቢው የሚገኙ ምእመናን በሰበካ ጉባኤ ተደራጅተው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ ቅዱስነታቸው የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ባገለገሉበት ጊዜ በአካባቢው በተለይም በጭልጋና በደባርቅ አውራጃዎች የነበረውን አለመረጋጋት ለማስተካከልና ሕዝቡ ሰላማዊ ኑሮውን እንዲቀጥል ለማድረግ እየተዘዋወሩ በማስተማር ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራሷን እንድትችል ለማድረግ ምእመናን በሰበካ ጉባኤ እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ሠርተዋል፤ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን የማስፋፋትና ቅርሶች በክብካቤ እንዲያዙ አድርገዋል፤ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ መንፈሳዊ መጽሔቶችና ጋዜጦች ለሕዝበ ክርስቲያኑ በየጊዜው አድርገዋል፤ የቤተ ክርስቲያን መመሪያና ደንብ (ቃለ ዐዋዲ) በተግባር እንዲተረጎም ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

በዕድሜ ብዛት የፈረሱና በከፊል የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱና በርካታ አዳዲስ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ አድርገዋል፡፡ በተለይም በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ፡- የአረጊት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በግል ገንዘባቸው ቆርቆሮ እንድትለብስ አድርገዋል፡፡ በዚሁ ወረዳ ውስጥ የምትገኘውን ደብረ ምሕረት ኪዳነ ምሕረትን ቤተ ክርስቲያን፣ እንዲሁ በግላቸው ዘጠኝ ሺህ ብር በማውጣት ቆርቆሮ እንድትለብስ አድርገዋል፡፡ መንፈሳዊ አዳሪ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ፣ የካህናት ማሠልጠኛዎች እንዲቋቋሙና ካህናት በተግባረ እድ የሚሠለጥኑባቸው ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

ምንም ዓይነት መተዳደሪያ ላልነበራቸው የአብነት መምህራን ወርኃዊ ደመወዝ እንዲቆረጥላቸውና መምህራኑ ሳይቸገሩ ዕውቀታቸውን ለትውልድ እንዲያስተላልፉ ከማድረግ ባሻገር የሀገረ ስብከቱ አገልጋዮች ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ ከፍተኛ የሆነ አባታዊ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም ለአንድ የዜማ መምህር፣ ለአንድ የቅዳሴ መምህር፣ ለአንድ ዕቃ ግምጃ ባለሙያ በድምሩ ለሦስት ሰዎች ከኪሳቸው ደመወዝ በመክፈል እንዲያገለግሉ አድርገዋል፡፡ ቅዱስነታቸው በጵጵስና ዘመናቸው አርባ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን የተከሉ ሲሆን በዕድሜ ብዛት የተጎዱ ፲፫፫ አብያተ ክርስቲያናትን ደግሞ አሳድሰዋል፡፡

በጋይንት አውራጃ በታች ጋይንት ወረዳ በምትገኘው በታላቋ ደብር ቤተ ልሔም ከአንድ በጎ አድራጊ ግለሰብ ርዳታ በመጠየቅ በናፍጣ የሚሠራ አንድ የሞተር ወፍጮ አቋቁመው ከወፍጮው የሚገኘው ገቢ ለካህናቱና ድጓ ለሚያደርሱ ተማሪዎች ወርኃዊ ደመወዝ እንዲሆናቸው አድርገዋል፡፡ በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ሊጋባ ቅዱስ ሚካኤል ለተባለው ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ ከበጎ አድራጊዎች በተገኘ ድጋፍ አንድ የሞተር ወፍጮ እንዲቋቋም አድርገው በዚህ ጥረታቸው አገልጋይ ካህናት የወር ደሞዝ እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡ ጥንታዊ መጻሕፍት ለትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ባደረጉት ጥረት፡- ሙሉ ሲኖዶስ፣ የቅዳሴ አንድምታና የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎችን ብራና ላይ እንዲጻፉ አድርገዋል፡፡ በጭልጋ፣ በሊቦ፣ በደብረ ታቦር፣ በጋይንት አውራጃዎችና በእስቴ ወረዳ የችግኝ ጣቢያዎች አቋቁመው በየዓመቱ በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ችግኞችን በማፍላት ለአብያተ ክርስቲያናት፣ ለግልና ለመንግሥት ድርጅቶች በማከፋፈል የተራቆቱ አካባቢዎች በችግኞች እንዲሸፈኑ አድርገዋል፡፡

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ በማኅደረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሐዲሳት ትርጓሜ፣ የድጓና የቅዳሴ ትምህርት ቤት አሠርተው ከዚያ የሚያስተምሩ መምህራን ወርኃዊ ደመወዝ እንዲከፈላቸው፣ ለደቀ መዛሙርቱ ደግሞ ድጎማ እንዲደረግላቸው አድርገዋል፡፡ ጥንታዊና ታሪካዊውን የጣና ቂርቆስ ገዳም በስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ወጭ እንዲታደስ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም ለሬማ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የአራት ሺህ ብር ድጋፍ አድርገዋል፡፡ የደረሞ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንንም ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ዐሥራ ዐራት ብር ወጭ በማድረግ አሳድሰዋል፡፡ እንዲሁም ጥንታዊውን የግርቢ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ስምንት ሽህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር ወጭ በማድረግም እንዲታደስ አድርገዋል፡፡ በአዘዞ በሰሚ ቅዱስ ሚካኤል ወደ ካህናቱ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት የሚወስደው መንገድ “በሥራ ለምግብ” መርሐ ግብር እንዲሠራ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪም የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም ጥበበ እድና የአዳሪ ትምህርት ቤት እንዲሠራ አድርገዋል፡፡ በጎንደር ጉባኤ ቤትና ክቡር ዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ የመቃብር ቤት የአራቱ ጉባኤያት ሥዕል እንዲሠራም አድርገዋል፡፡ በሊቦ አውራጃ በቆላ እብናት ለአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር የዐሥራ አምስት ሺህ ብር ድጋፍ አድርገዋል፡፡

በጎንደር ከተማ አዘዞ አባ ሳሙኤል ቤተ ክርስቲያን በመጠለያ ይረዱ ለነበሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ጋራ በመተባበር በኤልክትሪክ የሚሠራ ምጣድ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በዳባት ወረዳ የሚገኘውን የደፍቂ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርቲያንንና የቆማ ፋሲለደስን ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት አሳድሰዋል፡፡ ለአምስትያ ገዳምና ለጣርክ ማርያም የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ የዐደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን በከፍተኛ ወጪ እንዲታደስ አድርገዋል፤ የድምፅ ማጉያም አስገብተዋል፡፡ በጎንደር ዙሪያ አውራጃ ለሚገኘው ቸንከር ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ድጋፍም አድርገዋል፡፡ በዚያው በጎንደር ዙሪያ ከማክሰኝት እስከ አርባያ በለሳ ይሠራ ለነበረው የመንገድ ሥራ የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት የቆዳ፣ የሽመና፣ የሹራብ ሥራ፣ የልብስ ስፌት፣ የወፍጮና የዳቦ ቤት አቋቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ለስብከተ ወንጌል፣ ለሰንበት ትምህርት ቤቶችና ለሕዝብ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ አዳራሾችን ለበርካታ አብያተ ክርስቲያናት አሠርተዋል፡፡ ሕዝቡም ንጹሕ የመጠጥ ውኃ እንዲያገኝ የውኃ ጉድጓድ በማስቆፈር የበኩላቸውን ጥረዋል፡፡

በዓመታዊ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ቃለ ዐዋዲ ደንብ በትክክል እንዲፈጸም በማድረጋቸውና ሰበካ ጉባኤን በሚገባ በማደራጀታቸው በየዓመቱ በሚደረገው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ በተደረገው የአገልግሎት ውጤት ግምገማ መሠረት የጎንደር ሀገረ ስብከት ካሉት አህጉረ ስብከት መካከል ቅድሚያ ቦታ እንዲይዝ አድርገዋል፡፡ የኡጋዴን አውራጃ ሊቀ ጳጳስ ሆነው በተሾሙበት ወቅትም በሱማሌ ጦርነት ፈርሰው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትን አሳድሰዋል፤በጦርነቱ ምክንያት የተሸበረውንና የተደናገጠውን ሕዝበ ክርስቲያን በማጽናናት በሃይማኖቱ እንዲጸና፣ ሀገሩን እንዲወድ በማስተማር ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ ፍቅር ፈጽመዋል፡፡

ከዚያም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት በቀድሞ አጠራር ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ተዛውረው የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሁነው ተመድበዋል፡፡ ቅዱስነታቸው የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሁነው ሲመደቡ ሀገረ ስብከቱ ግን የራሱ ቢሮ አልነበረውም፡፡ የሊቀ ጳጳሱ መኖሪያ ቤትም አርጅቶ ነበር፡፡ በሊቀ ጵጵስና ዘመናቸው የመንበረ ጵጵስናውን ሕንጻ ከማሳደሳቸውም በተጨማሪ ከዐሥራ ሰባት በላይ ክፍሎችና አንድ ሁለገብ አዳራሽ አስገንብተው የሀገረ ስብከቱን ችግር አቃለዋል፡፡

# ተፈናቃይ ወገኖች ወደ አካባቢያቸው መመለስ ቢፈልጉም የደኅንነት ዋስትና የሚሰጣቸው አካል አልተገኘም

*በካሣሁን ለምለሙ*

ሀገራችን ኢትዮጵያ የደግነት፣የፍቅር፣የመተሳሰብና የአንድነት ምሳሌ ሆና ዘመናትን አሳልፋለች። በዚህም ምክንያት ሀገራችን በሌሎች ሀገራት ዜጎች እይታ መልካም ዝናና ተቀባይነት እንዲኖራት አስችሏታል። ዜጎቿ በሃይማኖትና በቋንቋ ልዩነት ሳይነጣጠሉ በፍቅርና በአንድነት ተከባብረውና ተዋደው ለበርካታ ዘመናት ከመኖራቸው ባሻገር ባንዳንና የውጭ ሀገር ጠላትን በተባበረ ክንድ ታግለው ጥለዋል።

ይሁን እንጅ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን የፖለቲካ ለውጥ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ከላይ የጠቀስናቸውን መልካም ዕሤቶች ሁሉ የሚያጠፋ እንግዳ የሆነ ባሕርይ መታየት ጀምሯል። ይኸውም ሰዎች በሃይማኖትና በብሔር ልዩነት ተከፋፍለው ሲጠፋፉ መመልከት የዕለት ተዕለት ተግባር እየሆነ መጥቷል። በዚህ የተነሳ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዚህ ሰዓት በዓለም ማኅበረሰብ ዘንድ የረኃብና የጦርነት ምሳሌ ሆና የምትጠራ ሆናለች። በሀገራችን ሕግና ሥርዓትን በሚጥሱ ወገኖች አማካይነት በየጊዜው በሚነሳ ጦርነት በርካታ ንጹሐን ለሞት፣ለአካል ጉዳትና ለስደት እየተዳረጉ ይገኛሉ። በሀገራችን ከመጣው የፖለቲካ ለውጥ ጋር ተያይዞ አመፅና ብጥብጥ ከተከሠተባቸው የሀገራችን ክፍሎች መካከል የከፋና ቤንች ማጂ ሀገረ ስብከት አንዱ ነው። በሀገረ ስብከቱ የሚኖሩ ምእመናን ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በሕገ ወጥ ታጣቂዎች በደረሰባቸው ተደጋጋሚ ጥቃት አብዛኛዎቹ ተገድለዋል፤ሌሎች ደግሞ አካባቢያቸውን ትተው ከመሰደድም አልፈው ከፍተኛ የሆነ የአካልና የሥነ ልቡና ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ከአካባቢያቸው ርቀው የተሰደዱ ወገኖችን ለመመለስና የተጎዱትንም ለመካስ በመንግሥት በኩል እየተደረገ ያለ ጥረት ባለመኖሩ ችግሩን የከፋና ተስፋ አስቆራጭ አድርጎታል። በእግዚአብሔር ጠባቂነት በሕይወት ተርፈው በተለያዩ ጊዜያዊ መጠለያ የሚገኙ ምእመናን በሕይወት የመኖር ዋስትና ሰጥቶ ወደ አካባቢያቸው የሚመልሳቸው አካል ይፈልጋሉ። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ባለፉት ሁለት ዓመታት ለከፋ ረኃብና ችግር እንደተጋለጡት ሁሉ ለተጨማሪ አደጋ ይጋለጣሉ። ምእመናንኑ ከዚህ ቀደም መልካም የሚባል ሕይወት ይመሩ የነበረ ቢሆንም ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ጀምሮ በተፈጸመባቸው ጥቃት ሀብት ንብረታቸው ተዘርፏል፤ ወድሟልም። በዚህ ወቅት መንግሥትና ሌሎች አካላት አስቸኳይ ድጋፍ ከላደረጉላቸው በዘላቂነት ለመቋቋም ከባድ ይሆንባቸዋል። በዛሬው የቃለ መጠይቅ እትማችንም በሀገረ ስብከቱ ስለደረሰው ጉዳት፣ ምእመናንን መልሶ ለቋቋም እየተሠራ ስላለውና መሠራት ስላለበት ጉዳይ ከከፋና ቤንች ማጂ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ



ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል የካፋ ሸካ እና ቤንች ማጂ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

የበላይ ጠባቂ ከሆኑት ከብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል ጋር አጭር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ።

ስምዐ ጽድቅ: - ከዚህ ቀደም በሰላሙ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የነበረው ሐዋርያዊ አገልግሎት፣ የልማት እንቅስቃሴና የምእመናን የኑሮ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?

ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል:- በሀገረ ስብከቱ ሥር የሚኖረው ሕዝበ ክርስቲያን ከዚህ ቀደም ወልዶ ከብዶ ንብረት አፍርቶ በመቻቻል፣በመተዛዘንና በመረዳዳት የሚኖር ነበር። የመንግሥት ሠራተኛው ሕዝብን በታማኝነት አገልግሎ ይኖራል፤ነጋዴውም ነግዶ ያተርፋል፤ተማሪውም በሚማረው ትምህርት ሀገርን ሊጠቅም በርትቶ ይማራል፤ እንዲሁም ገበሬው የሰጡትን ሁሉ በሚያበቅለው የአካባቢው መሬት አርሶ አምርቶ ይኖራል። አካባቢው እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዓመቱን ሙሉ ዝናብ የማይለየው፣ ለምለም፣መንፈስን የሚያድስና የሰጡትን ሁሉ የሚያበቅል በመሆኑ የአካባቢው ገበሬዎች ትርፍ አምራች የሚባሉ ናቸው። በዚህ የተነሳ ምእመናን መጽናኛና ኀዘን መርሻ ለሆነችው ቅድስት

ቤተ ክርስቲያን ሳይሰስቱ ያላቸውን ሁሉ ይሰጣሉ። አገልግሎቷንም በሁሉም ዘርፍ በመደገፍ ዐሥራታቸውን ያወጣሉ፤ ክርስቲያናዊ ግዴታቸውንም ፍጹም በሆነ መንፈሳዊ ተነሳሽነት ይፈጽማሉ።

በተለያየ የሙያ ዘርፍ የተሠማሩ ምእመናን ክርስቲያናዊ ድርሻቸውን መወጣታቸው በሀገረ ስብከቱ የነበረውን የልማትና ስብከተ ወንጌል አገልግሎት የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አግዟል። ይህ በመሆኑም በየጊዜው ዘማሪና መምህራነ ወንጌልን ከአዲስ አበባና ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በመጋበዝ የአካባቢውን ሕዝበ ክርስቲያን የወንጌል ጥማት ማርካት ተችሏል። ማኅበረ ምእመናንም በሚያገኙት ምግበ ነፍስ እረክተው ሕይወታቸውን በፈቃደ እግዚአብሔር እየመሩ ሥጋወደሙን በመቀበል የክብሩ ወራሽ የስሙ ቀዳሽ ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያን ለልማት አገልግሎት የሚውሉ ሕንጻዎች እንዲኖራትና በዕድሜ ብዛት የተጎሳቆሉ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲጠገኑ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በሌላቸው አካባቢዎች አዳዲስ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ የቻሉትን ሁሉ ሲያደርጉ ቆይተዋል።

በተጨማሪም በርካታ ምእመናን ኵላዊት በሆነች አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጸንተው ያልጸኑትንና የሚቅበዘበዙትን የሚያጸኑና ወደ እውነተኛውና ቀጥተኛው መንገድ የሚመልሱ ሆነዋል። በየአጥቢያው ያሉ አገልጋዮችም ያለድካም ሌሊትም ቀንም ሳይሉ ማኅበረ ምእመናንን በቅንነት በማገልገል እውነተኛ አገልጋይና የመንጋው እረኛ መሆናቸውን አስመስክረዋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ከሀገራችን የፖለቲካ ለውጥ ጋር ተያይዞ በሀገረ ስብከቱ የተፈጠረ መከራ እንዳለ ይታወቃል፤ እስኪ በሀገረ ስብከቱ የተፈጠረውን ችግር በዝርዝር ያስረዱን?**

**ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል፡-** ሀገራችን ኢትዮጵያ የሰላም፣የመቻቻልና የፍቅር ተምሳሌት መሆኗ ሁሉ የሚያውቀው ሀቅ ሆኖ እያለ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ወንድም በወንድሙ ላይ ሰይፍ የሚያነሳበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ሃይማኖት በሃይማኖት ላይ አንዱ ብሔር በሌላው ብሔር ላይ የሚያምጽበትና ለመጠፋፋት ቦታና ጊዜ የሚጠብቁበት ሁኔታ መፈጠሩ እግዚአብሔር በምሕረቱ ካልጎበኘን በስተቀር መጪው ጊዜ እጅግ ከባድ ነው የሚሆነው። ሀገራችን ለሁላችን የምትበቃ ሁና ሳለ ጎራ ለይቶ ለመጠፋፋት መነሣሣት የሰይጣን እንጂ የሰው ልጅ ሥራ ምግባር አይደለም።

በሀገራችን በተለይ ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ በየአካባቢው እየታየ ያለው ዐመፀኝነትና ሥርዓት አልበኝነት በወንድማማቾች መካከል ከባድና የማያበራ እልቂት አስከትሏል። የሰው ልጅ በሃይማኖቱና በብሔሩ ካባ ውስጥ ገብቶ ሲጠፋፋ መመልከታችን ለሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የማይመጥን ተግባር ሆኖ እናገኘዋለን። በሀገራችን የፖለቲካ ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በየቀኑ የምንሰማው መከራና እልቂት ብቻ ሆኗል። በሰሜን፣በደቡብ፣በምዕራብና በመሥራቅ ያለው ሕዝባችን የሞትና ረኃብ ጥላ ካንዣበበት ውሎ አደድሯል። ከፈጣሪው ውጭ ከረኃብ መንጋጋ ውስጥ ያወጣኛል ከጦርነት ይገላግለኛል ብሎ የሚተማመንበት በዚህ ሰዓት አንድም ኃይል የለም።

በደቡብ የሀገራችን ክፍል በተለይ በቤንች ማጅ ዞን ጉራ ፈርዳ ወረዳ ከለውጡ በፊት አልፎ አልፎ በሕዝብ መካከል አለመረጋጋት ቢከሠትም ከለውጡ በኋላ በሕዝባችን ላይ የመጣው መከራ ግን በሰው ልጅ አእምሮ ሊጠፋ የማይችል ነው። ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ንጹሓን ያለበደላቸው በታጣቂዎች ተጨፍጭፈው በጅመላ መቃብር ይቀበራሉ። ዕድል ቀንቷቸው ሕይወታቸውን ያተረፉ ሰዎች ደግሞ ለዘመናት ልጅ ወልደው አሳድገው በኖሩበት አካባቢ ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ለወንበዴ ትተው እግራቸው ወደአመራቸው ይሰደዳሉ።

ወንበዴውም የሚፈልገውን ወስዶ ያለፈልገውን መስኪኖቹ ከሠሩት የአንገት ማስገቢያ ጎጆ ጋር በእሳት ያነደዋል። ጉራ ፈርዳ ላይ የሆነው ይህ ተግባር ነው። ምእመናን በእርሻና በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተሰማርተው የተመቼ ኑሮ ከመኖር አልፈው የተቸገሩ ወገኖቻቸውን የሚረዱ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚደግፉ ነበሩ። አሁን ያን ሁሉ ለማድረግ ተቸግረዋል፤ምክንያቱም ግማሹ አካባቢውን ጥሎ ተሰዶ አቅራቢያው በሚገኝ ወረዳዎች የሰው ልጅን ምጽዋት የሚጠብቅ ሆኗል። ሌሎቹ ደግሞ ሰው በመሆናቸው ብቻ እንዲሞቱ ተፈርዶባቸው በጅምላ ተገለው በጅምላ ተቀብረዋል። ከሞት ተርፈው በተለያዩ አካባቢዎች በመጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙም ወደቀደም አካባቢያቸው እንዳይመለሱ በሕይወት የመኖር ዋስትና የሚሰጣቸው አካል አልተገኘም። በዚህ ምክንያት በአሁን ሰዓት ከዚያ ያለችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አወዳሽ ቀዳሽና ምእመናን አጥታ ተዘግታ ጥገኛለች። እስካሁን ድረስ በተለያዩ አካባቢዎች ከሃያ አምስት በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው ይገኛሉ።

ወልደው ከብደው፣ተግባብተው በፍቅር እምነታቸውን ጠብቀው በሚኖሩበት አካባቢ አገልጋዮች ግማሾቹ እንደ ዱር አውሬ ታድነው ተገለዋል፤ሌሎች ደግሞ "ከመሞት መሰንበት" ብለው ሰላም ወዳለበት አካባቢ ሄደው ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል እየተጉ ሚገኙ ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ የመከራውን ጽዋ በድፍረት ለመጎንጨት በአካባቢያቸው የቀሩ አሉ። ስለሆነም በስደት ላይ ያሉ ምእመናን በሕይወት የመኖር ዋስትና ተሰጥቸቷው ወደ አካባቢያቸው ቢመለሱ መልካም ነው። ርዳታን ጨምሮ የወደሙና የተዘረፉ ንብረቶቻቸው ተመለሰውላቸው ወደቀደመ ሰላማዊ ኑሯቸው ተመልሰው አካባቢያቸውንና ሀገራቸውን የሚጠቅሙበት መንገድ እንዲመቻች ፈቃደ እግዚአብሔርን እንጠይቃለን።

ከዚህ ቀደም በሀገረ ስብከትና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ምእመናን የደኅንነት ከለላ እንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል። ችግሩ ከተከሠተ በኋላም ርዳታ ከምእመናን በመሰብሰብ ለተፈናቃይ ወገኖች የዕለት ርዳታ ስናደርስ ቆይተናል። ያ ሁሉ ግን በቂ ሆኖ አልተገኘም። ምእመናንን በዘላቂነት ከችግራቸው ማላቀቅ

አልተቻለም፡፡ ለተፈናቀሉ ምእመናን ተጨማሪ ርዳታ ለማቅረብና ወደ አካባቢያቸው ለመመለስ ብርቱ ሥራ ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁሉም ድረሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በዚያ አካባቢ ለምእመናን መፈናቀልና ሞት ምክንያት የሆነው አካል ማነው ይላሉ?**

**ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል፡-** ለምእመናን ሞትና ሥቃይ መንሥኤ የሆነው የሀገሪቱ የፖለቲካ ለውጥ ይዞት የመጣው ጽፈኝነትና አክራሪነት ነው፡፡ "ከእኔ ብሔርና ሃይማኖት ውጭ ሌላ ሰው በእኔ አካባቢ መኖር የለበትም" የሚሉ ጽንፈኛ ኃይሎች በየጊዜውና በየአካባቢው መፈጠራቸው ለንጹሓን ወገኖች ሞትና መፈናቀል ምክንያት ሆኗል፡፡ አንዳንድ ጊዜም የመዋቅርና ፖለቲካ ጥያቄ ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች "ንጹሓንን መጨፍጨፍና ማፈናቀል ጉዳያችን በመንግሥትና በሕዝብ ዘንድ ትኩረት ያስገኛል" ብለው የሚያስቡ አሉ፡፡ ስለሆነም በርካታ ንጹሓን ዜጎች ያለበደላቸው በጭካኔ ይገደላሉ፤ይሰደዳሉ፡፡ በጉራ ፈርዳ ወረዳም በንጹሓን ምእመናን ላይ ጭካኔ የተሞላበት ግድያና የማፈናቀል ተግባር የሚፈጽሙት መሰል ዓላማ ያነገቡና በአካባቢያቸው "የእኔ" ከሚሉት ብሔርና ሃይማኖት ውጭ እንዲኖር የማይፈቅዱ አካላት ናቸው፡፡ በዋናነት ከመንግሥት ቁጥጥርና አቅም በላይ ያልሆኑ ታጥቀው በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ አካላት የሞትና የመፈናቀል መንሥኤዎች ናቸው፡፡ በዚህ ሳቢያ በርካቶች ወልደው ከብደው፣አርሰውና ነግደው ዘመናቸውን ሁሉ አካባቢውን አልምተው የኖሩ ምእመናን ያለተከላካይ በጭካኔ ተገለዋል፤ከቤታቸውና ከሀብት ንብረታቸው ተለይተው ግማሾቹ በቤተ ክርስቲያን ሌሎቹ ደግሞ በየትምህርት ቤቱ በጊዜያዊነት ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አካላት ከመፈናቀላቸውና በግፍ ከመገደላቸው በፊት በኢኮኖሚ ከራሳቸው አልፈው ለሌላው የሚተርፉ የነበሩ ናቸው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በምእመናንና በንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት ምንድን ነው?**

**ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል፡-** ከችግሩ ስፋትና ውስብስብነት አንጻር የደረሰውን ጉዳት ለመግለጽ እጅግ ከባድ ነው፡፡ ምእመናን ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያፈሩት ሀብትና ንብረት በአንድ ጀንበር ወድሟል፤ተዘርፏል፡፡ ስለሆነም በዚህ ወቅት ምእመናን የሰው እጅ ጠባቂ ሆነዋል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስከፈትና የተፈናቀሉ ምእመናንን ወደመኖሪያ አካባቢያቸው ለመመለስ ምን እየተሠራ ነው?**

**ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል፡-** የተዘጉ አብያተ ክርስቲያንትን ለማስከፈት ሀገረ ስብከቱ ጥረት እያደረገ ሲሆን የተፈናቀሉ ምእመናን ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱም ከወረዳ እስከ ዞን ያሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን እየተማጸነ ይገኛል፡፡ የፈረሰውን የሚሠራ የወደመውን የሚተካ ብቻ ሳይሆን ምእመናን ወደአካባቢያቸው ከተመለሱ በኋላም ከታጠቁ ኃይሎች ሽብር የሚጠብቃቸውና የሕይወት ዋስትና የሚሰጣቸው የመንግሥት አካል ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ተፈጻሚ እንዲሆን ደግሞ ሀገረ ስብከቱም ሆነ አጠቃላይ እንደቤተ ክርስቲያን መጠነኛ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን ሰሚ ጆሮ አስተዋይ ልቡና ባለመኖሩ ችግሩ ከተፈጠረ ጀምሮ ለመንግሥት አካላት ያቀረብናቸው አቤቱታዎች ሁሉ አንዱም ምላሽ አላገኘም፡፡ ለበርካታ ጊዜያት የምእመናን ችግር እንዲፈታ ብዙ ጥረናል፤ደክመናል፤አሁንም በጥረት ላይ እንገኛለን፡፡ በጸጥታ ችግር ምክንያት ከሁለት ዓመት በላይ አካባቢያቸውን ጥለው በየአካባቢው ተሰደው ያሉ ወገኖችን መመለስና በሕይወት የመኖር ዋስትና የመስጠት ኃላፊነት የሀገሪቱ መንግሥት በመሆኑ ችግሩ እስኪፈታ ድረስ መጠየቃችንን እንቀጥላለን፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በየጊዜው በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጥቃትና በደል እየደረሰ ይገኛልና ይህንን ድርጊት ለማስቆም ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል፡-** የችግሩ መፍቻ ቁልፍ በዋናነት ያለው በሀገሪቱ መንግሥት እጅ ነው፡፡ በሀገሪቱ የዜጎች ሰላምና ደኅንነት እንዲረጋገጥ በአባትነት መንፈስ በተደጋገሚ ጠይቀናል፡፡ ሀገራችንን እየመራ ያለው መንግሥት ሕዝብ በምርጫ የመረጠው ሰላምና ደኅንነቱን ያስጠብቅለኛል እንዲሁም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱን ያረጋግጥልኛል ብሎ እስከሆነ ድረስ መንግሥት በዋናነት በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ላይ በየጊዜው የሚደርሰውን ጥቃት የማስቆም ኃላፊነት አለበት፡፡ በሀገራችን መተዳደሪያ ሕግ መሠረት ወንጀለኛ በፈጸመው ወንጀል ልክ መንግሥት ቅጣቱን ሊሰጠውና የተበደሉ ዜጎቹንም እንደየጉዳታቸው መጠን ሊክሳቸው ይገባል፡፡

ሕግና ሥርዓት የማይከበርና ሁሉም ሰው ከሕግ በታች የማይሆንበት አሠራር ካለ ደግሞ ሀገራችን የወንበዴ መፈንጫና አቅም ያለው በሌለው ላይ ጫና የሚያሳድርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለተፈናቀሉ ምእመናንና ለተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት ድጋፍ ሊያደርጉ ለሚችሉ ወገኖች የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድን ነው?**

**ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል፡-** ተፈናቅለው በየአካባቢው ተጠልለው ለሚገኙ ምእመናን ለጊዜው የዕለት ቀለብ የዓመት ልብስ የሚያገኙበት መንገድ ቢፈለግ መልካም ነው፡፡ የተዘጉ ከሃያ አምስት በላይ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስከፈት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ ምእመናንና ኢትዮጵያውያን የበኩላቸውን ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በስደት ላይ ያሉ ካህናትም የደኅንነት ዋስትና እንዲያገኙ ሁሉም ወገን ለመንግሥት ድምጹን ሊያሰማ ይገባል፡፡

# ሰሙነ ሕማማት

ሄለን ገነነ

ሰላም ልጆች! እንደምን ከረማችሁ? አሜን የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን፡፡ ልጆች ዛሬ የምናስነብባችሁስለ ሰሙነ ሕማማት ሥርዓትና ትርጓሜ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን ጾም ምን እንደሆነ ታውቃላች? ጎበዞች! ጾም ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸውና ለሰውነት ምቾት ከሚሰጡ ነገሮች መታቀብ ማለት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጾም በሠራችው ሕግ መሠረት ሰባት የአዋጅ አጽዋማት አሉ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕድሜው ከሰባት ዓመት በላይ ያለ ሁሉ እነዚህን ሰባት አጽዋማት እንዲያሟቸውም ሕግ ሠርታለች፡፡ ከእነዚህም አጽዋማት ዐብይ ጾም ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ ለ፰(ስምንት) ሳምንት ያህልም ይጾማል፡፡ ልጆች! እናንተም ሰባት ዓመት ከሞላቹ ጾም መፆም የሚገባ ነው፡፡ ታዲያ በምትጾሙበት ወቅት ከምግብና መጠጥ ብቻ ሳይሆን መልካም ሥራዎችን መሥራትም ይገባናል፡፡ ታላላቆቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን እንዲሁም የሃይማኖት አባቶች የሚሉትን ልትሰሙና ልትታዘዙም ያስፈልጋል፡፡



እጽበተ እግር

ሰሞነ ሕማማት የሚለው ሐረግ ከሁለት ቃላት የመጣ ሲሆን እነሱም ሰሙነ እና ሕማማት የሚሉት ናቸው፡፡ ‹ሰሙነ› ማለት ሳምንት ማለት ሲሆን ሕማማት ደግሞ ‹ሐመ› ከሚል የግዕዝ ግስ የወጣ ‹ታመመ› የሚል ትርጉም የሚሰጥ ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች! ሰሙነ ሕማማት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕመሙንና ሞቱን የምናስብበት የምንዘክርበት የዐብይ ጾም የመጨረሻ ሳምንት ነው፡፡ ሰሙነ ሕማማት ከዕለተ ሆሣዕና ማግስት እስከ ትንሣኤ ሌሊት ያለውን ጊዜና ቀናት ያመለክታል፡፡

ልጆች! የሰሙነ ሕማማት ቀናቶች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሳያድነን በፊት የነበሩትን ወይም ዓመተ ፍዳ በመባል የሚጠሩ ጊዜያቶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በዚህ ሳምንት ክርስቲያኖች የክርስቶስን ውለታ እያሰቡ እጅግ የሚያዝኑበት፣ የሚያለቅሱበት አምላካቸውን የሚማጸኑበት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚገኝ ሳምንት ነው፡፡ ታዲያ ልጆች! በዚህ በሰሙነ ሕማማት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የተለያዩ የሚፈጸሙና የማይፈጸሙ ሥርዓቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የቤተ ክርስቲያኒቱ የዘወትር አገልግሎት የሆነው ጥምቀተ ክርስትና፣ ሢመተ ክህነት፣ ሥርዓተ ፍትሐት፣ ሥርዓተ ተክሊልና ሌሎችም የተለመዱ አገልግሎቶች አይካሄዱም፡፡ በመስቀል መባረክ፣ ኑዛዜ መስጠትና መቀበል፣ እግዚአብሔር ይፍታህ ማለት አይኖርም፡፡ በሰሙነ ሕማማት ምዕመናን እርስ በእርስ በመሳሳም ሰላምታ አይለዋወጡም፡፡ ይህም ይሁዳ ጌታችንን በመሳም አሳልፎ ስጥቷልና ያንን ለማሰብ ነው፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች አስቀድሞ በሆሣዕና ዕለት ይከናወናሉ፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማይታሰብበት ጊዜ ባይኖርም የዓብይ ጾም መዝጊያ ሳምንት የሆነው ሰሙነ ሕማማት ግን ከፍተኛውን ሥፍራ ይይዛል፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ሥርዓታት የጌታችንን ሕማሙን፣ ሥቃዩን፣ መከሰሱን፣ መያዙን፣ ልብሱ መገፈፉን፣ በቀራንዮ አደባባይ መቆሙን፣ መስቀል ላይ መዋሉን፣ ሐሞት መጠጣቱንና ሌሎችንም ለበደለኛው የሰው ልጅ ሲባል የተከፈለውን በሚያስታውሱ አገልግሎቶች ይተካሉ፡፡ ካህናትና ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ተሰብስበው አብዝተው በመጾም፣ ከሃሜት፣ ከነገር፣ በአጠቃላይ ከኃጢአት ርቀው የሕመሙን ነገር የሚያወሱ መዝሙሮች በመስማትም ጭምር ያሳልፋሉ፡፡ በዚህ ሳምንት ውስጥ የጌታችንን መከራውንና ድካሙን የሚያስታውሱ እንደ ትንቢተ ኤርምያስ፣ ትንቢተ ኢሳይስ እንዲሁም መዝሙረ ዳዊት ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይነበባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ልጆች! በሰሙነ ሕማማት በቤተ ክርስቲያን ግብረ ሕማማት የተባለ መጽሐፍ ይነበባል፡፡

ግብረ ሕማማት ማለት የሕማም፣ የመከራ ሥራ ማለት ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳምና ለዘሩ መዳን የተቀበለውን መከራ የሚዘክር መጽሐፍ ነው፡፡ የጌታችን መከራውን ስቃዩንና ሕማሙን በሰዓትና በጊዜ ከፍሎ በዝርዝር የሚገልጽ

በመሆኑ የጌታችን ሕማም በሚታሰብበት በሰሙነ ሕማማት ወቅት በዋነኛነት አልግሎት ላይ የሚውል በመሆኑ ግብረ ሕማማት ተባለ፡፡



**የሰሙነ ሕማማት ቀናትና ትርጉማቸው**

ልጆች! አሁን ደግሞ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ ያሉትን ዕለታት እና በዕለታቱ የተከወኑትን ድርጊቶች እንመልከት፦

**ሰኞ፡-** መርገመ በለስ የተፈጸመበት ዕለት ነው፡፡ ጌታችን ከቢታንያ ሲወጣ ተራብ ቅጠል ያለባትን በለስ ተመልክቶ ወደ በለሲቱ ሲቀርብ ከቅጠል በቀር ምንም ፍሬ ባለማግኘቱ ‹‹ከአሁን ጀምሮ ለዘለዓለም ማንም ከአንቺ ፍሬ አይብላ›› (ማር.፲፩፥፲፬) በማለት ስለረገማት‹‹ መርገመ በለስ የተፈጸመባት ሰኞ በመባል ትታወቃለች፡፡ ልጆች! ሰኞ አንጽሖተ ቤተ መቅደስም ተብሎ ይጠራል፡፡ ጌታችን ወደ ቤተ መቅደስ ሔዶ በቤተ መቅሱ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን ‹‹ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል ፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት›› (ማቴ. ፳፩፥፲፫) በማለት ገርፎ ከቤተ መቅደሱ ያስወጣበት ቀን በመሆኑ ‹‹አንጽሖተ ቤተ መቅደስ›› ይባላል፡፡

**ማክሰኞ፡-** የጥያቄ ቀን ይባላል፡፡ አይሁድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰኞ ዕለት በቤተ መቅደሱ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን እየገረፈ ከቤተ መቅደሱ በማስወጣቱ ምክንያት‹‹ በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ? ይህንንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ?›› (ማቴ. ፳፩፥፳፫) ተብሎ በካህናት አለቆች የተጠየቀበት ቀን በመሆኑ የጥያቄ ቀን ተብሏል፡፡ ልጆች ከዚህም በተጨማሪ ማክሰኞ የትምህርት ቀን ይባላል፡፡ ጌታችን በዕለቱ በቤተ መቅደስ ረጅም ትምህርት ስላስተማረ ነው፡፡

**ረቡዕ፦** ምክረ አይሁድ ይባላል፡፡ በዚህ ዕለት የአይሁድ ሊቃነ ካህናትና ጸሐፍት ጌታችንን እንዴት መያዝ እንዳለባቸው የመከሩበት ቀን በመሆኑ ነው፡፡ ልጆች ዕለተ ረቡዕ የመልካም መዓዛ ቀንም ይባላል፡፡ መላ ሕይወቷን በኃጢአት ያሳለፈችው ማርያም እንተ እፍረት(ባለ ሽቶዋ ማርያም) ስለኃጢአትዋ ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ የአልባስጥሮስ ሽቶ አምጥታ በጌታ ራስ ላይ ስላርከፈከፈችው (ማቴ.፳፮፥፯) የመልካም መዓዛ ቀን ይባላል፡፡

**ሐሙስ፡-** ጸሎተ ሐሙስ ይባላል፡፡ ጌታችን በአይሁድ ጭፍሮች ከመያዙ በፊት በጌቴሴማኔ የአትክልት ስፍራ ሲጸልይ በማደሩ (ማቴ. ፳፮፥፴፮) ጸሎተ ሐሙስ ይባላል፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ዝቅ ብሎ ያጠበበት ቀን በመሆኑም(ዮሐ.፲፫፥፩-፲፩) ሕጽበተ ሐሙስ ይባላት፡፡ የቅዱስ ቁርባን ምሥጢር የተከናወነበት ዕለት በመሆኑም የምሥጢር ቀን በመባል ይታወቃል(ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፱)፡፡

**ዓርብ፡-** የስቅለት ዓርብ ይባላል፡፡ በዚህ ዕለት ጌታ በመስቀል ላይ ለሰዎች ሲል የተሰቀለበትና በሥጋው መከራን ተቀብሎ የሞተበት ነው (ማቴ.፳፯፥፴፭)፡፡

**ቅዳሜ፡-** ቀዳም ስዑር ትባላለች፡፡ የተሻረች ቀዳሚት ሰንበት ትባላለች፡፡ ስዑር መባሏ በዓመት አንድ ቀን ስለምትፆም ነው፡፡ ጌታችን የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ፈጽሞ በመቃብር አርፎ የዋለባት ዕለት ናት፡፡

**እሑድ፡-** ዕለት ትንሣኤ ይባላል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣበት ዕለት ነው፡፡ ሁሉም ክርስቲያን በየቤቱ በዓሉን ከቤተሰቡ ጋር ደስ ብሎት የሚከብርበት ለክርስቲያኖች የተከበረችና ልዩ ቀን ናት፡፡

ልጆች! ስለ ሰሙነ ሕማማት እና ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉትን ቀናት በተመለከተ በደንብ እንደተረዳችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ በሌላ ጽሑፍ እስክንገናኝ ደኅና ሁኑ፡፡

# ቅዱሱን በዓል እንዴት እናክብረው?

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቤት ነች፤ የደስታ ቤት ነች፤ የዕረፍት ቤት ነች፡፡ ጾሙ ብቻ ሳይሆን በዓሉም በሥርዐት የተሠራ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ከጾም ብቻ ሳይሆን ከበዓለትም በረከት እንዲያገኙ ቤተክርስቲያን ትፈልጋለች፡፡ ጾም ለክርስቲያኖች ሕይወት መታነጽ አስተዋጽኦ እንዳለው ሁሉ በዓላትም አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ሆነው በሥርዐት እንዲከበሩ ይፈለጋል፡፡

ቤተክርስቲያናችን ከምታከበራቸው በዓላት ሁሉ ደግሞ ታላቅ ሆኖ በእጅጉ በሰፊው የሚከበረው በዓለ ትንሣኤ ነው፡፡ በዓለ ትንሣኤ ዐውድና ስሜት በእጅጉ ሰፊ ነው፡፡ ዐቢይ ጾም በእጅጉ ከብሮ በብዙ ሥርዐት እንደሚጸመው ሁሉ በዓለ ትንሣኤም በልዩ ልዩ መልክና ቅርጽ ደምቆ የሚከበረው እስከ በዓለ ሃምሳ/በዓለ ጰራቅሊጦስ ድረስ ነው፡፡ የክብሩ ታላቅነት የብርሃኑም ጸዳል በእጅጉ ሰፊ ነው፡፡

በዓለ ትንሣኤ አስቀድሞም በነቢያት በአበው ተስፋ ሲደረግ የነበረ የነጻነት በዓል ነው፡፡ (ዘኁ ፱÷ ፪፣ ናሆ ፩÷ ፲፭) ይህ ታላቅ ፋሲካችን ደግሞ ክርስቶስ መሆኑን ሐዋርያው መስክሮልናል፡፡ የክርስቶስ ትንሣኤ ደግሞ ነፍሳችንንም ሥጋችንንም ያከበረ፣ ነጻ ያወጣ የማዳን ሥራው ስለሆነ ክርስቲያን ሁሉ በታላቅ ደስታ ሊያከብረው የሚገባ ሆኗል፡፡

ስለዚህ ክርስቲያኖች በዝማሬ፣ ቃሉንም በመመስከር በበርካታም የበዓል መገለጫ በሆኑ መንፈሳዊ ተግባራት ያከብሩታል፡፡ ምግብ ለሥጋችን ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንም የሚገባትን በቂ ምግብ በመመገብ የምትከበርበት በዓል ነው፡፡

ነፍስ የምትፈልገው የራሷ በዓል ማክበሪያ ማዕድ አላት፡፡ ‹‹በእምነትና በተከተልኸው በመልካም ትምህርት ቃል የምትመገብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ፡፡›› (፩ኛ ጢሞ ፬ ÷ ፮) እንደተባለ ቃሉን አብዝታ መስማት የምትፈልግበት ጊዜ ነው፡፡ ነፍሳችን መብላት የምትፈልገው ምድራዊ መጠጥን ምድራዊ መብልን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊውን ማዕድ ቅደሱስ ስጋውን ክቡር ደሙን ዳግመኛም የመላእክትን ምግብ ምሥጋና ነው ‹‹የመላእክትንም እንጀራ ሰው በላ፤›› (መዝ. ፸፯÷፳፭) እንደተባለ፡፡ መላእክት በጋራ የሚሳተፉበት ማእድ ደግሞ የዝማሬ የምስጋና ማእድ ነው፡፡ ለነፍስም ለበዓል ማክበሪያም የሚያስፈልገው ይህ ዝማሬ ነው/ ምስጋና ነው፡፡ መጽሐፍም ‹‹ይህን ሳስብ ነፍሴ በእኔ ውስጥ ፈሰሰች፥ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ምስጋና መኖሪያ ስፍራ እገባለሁና፤ በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና ምስጋና ቃል አሰሙ፡፡›› (መዝ. ፵፪÷፭) ይላል፡፡

ነፍሳችን በታላቅ ፍቅርና ትህትና በዓሉን ታከብራለች፡፡ ከሰዎች ጋር አብረን በመሰብሰብ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፤ እንግዶችን አክብረን እንቀበላለን፣ እንጋብዛለን፣ ድሆችን በበዓሉ እንዳያዝኑ ደስታን እንዲድርጉ ርህራሄን እንዳርጋለን፡፡ እርስ በእርስ በመስማማት በይቅርታ፣ በእርቅ እርስ በእርስም በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም እየተባባልን እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኘውን በማድረግ እናከብራለን፡፡ የክርስቲያን ነፍስ ምግቧ ፈቃዱን መፈጸም ነውና ጌታ ስለራሱ ሲናገር ‹‹የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው፡፡ ›› ባለው ቃሉ ማስተዋል ይቻላል፡፡ (ዮሐ. ፬÷፴፬) ፡፡

በዓላችን ክርስቶስና ክርስቶሳዊ የሆነው ነገር ሁሉ ነው፡፡ (ማቴ. ፳፭ ÷ ፳፫) ለዚህ ታላቅ የደስታ በዓል የጌታ ደስታ ታዳሚ፣ ተሳታፊ ሊሆን የሚገባው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚያከብር፣ የሚታዘዝ ታማኝ አገልጋይ ነው፡፡ ‹‹አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው፡፡›› (ማቴ. ፳፭÷ ፳፩) እንዲል፡፡

ይህ በመሆኑም ጾመ ድኅነት እንኳን የሚጾምበት ሥርዐት በሃምሳው ቀናት ውስጥ ይሻራል፡፡ በአባቶቻችን ልማድም በገናዎቻችንን ሰቅለን ከበሮዎቻችንን እናነሣለን፡፡ የምንለብሰውም ጸኣዳ፣ የምንዘምረውም በእልልታ ይሆናል፡፡ የኀዘን የትካዜ ድባቦች አይኖሩም፡፡ እነዚህን ሁሉ ለጊዜው ያዝ አድርገን የክርስቶስን የትንሣኤውን ኃይል ሰዎችም ያገኙትን ዕርፍትና ደስታ ከፍ ከፍ እናዳርጋለን፡፡

በዓሉ የደስታ ነው ብለን ስናበቃ አንዳንድ ወገኖች ግን ደስታን በሚተረጉሙበት መንገድ ነፍሳቸውን ሲወጉ እናያቸዋለን፡፡ ቤተ ክርስቲያን ደስታ አድርጉ ስትለን ነፍሳችን በሚጠፋበት፣ ከክርስቶስ ህግና ሥርዐት በምናፈነግጥበት መንግድ እንድንሄድ

እየፈቀደችልን አይደለም፡፡ ቤተክርስቲያን ደስታ አድርጉ ስትል ነፍሳችን የምትድንበት፣ ሕይወታችን የሚታነጽበትን መንፈሳዊ ደስታ ማለቷ ነው፡፡

በርካቶች በማይገባ መንግድ በዓለ ትንሣኤን እስከ በዓለ ሃምሳም ያለውን ጊዜ ያሳልፋሉ፡፡ ብዙውን ጊዜያቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች በዘፈን፣ በጭፈራ ያሳልፋሉ፡፡ በርካታ ጊዜያቸውን በመስከርና አልኮል መጠጥ አዘውታሪ በመሆን ያሳልፋሉ፡፡ የዝሙት/የማመንዝር ነገሮች ሁሉ ይስፋፋሉ፡፡ በዓሉ ከንቱ ሥጋዊ ፍትወታትን ሁሉ ለመፈጸም የምንለቀቅበት ጊዜ አድርገው የሚያስቡ አሉ፡፡ ሥጋችንን በመብል በመጠጥ ብቻ የምናደልብበት ወቅት ከተደረገ ለሥጋችን ነፃነት ሠጥተን በዓሉን ማቃለል ሆኗል፡፡

የደስታ የበዓል ትርጉም የተዛባባቸው ብዙ ናቸው፡፡ በደስታ (በዓል) እና ኃጢአት መካከል ያለው ድንበር የጠበበባቸው የጠፋቸውም በርካቶች አሉ፡፡ በዓል ለኃጢአት መለለቀቅ ሆነባቸው ብርካቶች አሉ፡፡

የምንታዘበው ግን በዐቢይ ጾም የበረቱ ሰዎች በሃምሳዎቹ የበዓል ቀናት ሲዳከሙ፣ በዐቢይ ጾም ብርታት መንፈሳዊ ፍሬዎችን ያፈሩ ሰዎች በበዓሉ ጊዜ ፍሬቸውን ሲያረግፉ፣ በሃይማኖት ጥብቅ ሆነው የቆዩ ሰዎች ሲላሉ ይታያሉ፡፡ ከአልኮል ርቀው የቆዩ ሰዎች ሰክረው ለትፋት እስከሚጋለጡ ይጠጣሉ፡፡ ራሳቸውን በጾም ገርተው የቆዩ ሰዎች በቁንጣን ሲጎዱ ይታያሉ፡፡ ሲያስቀድሱ ሲተጉ የነበሩ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ይጠፋሉ፡፡ ይህን በቅርብት በብዙዎች ወንድሞቻችንንና እህቶቻችን ሕይወት ውስጥ ፈተና ሆኖ ሲመጣባቸው ይስተዋላል፡፡

እስራኤል በበረሃው ተጉዘው በታላቅ ተጋድሎ ወደፊት ተራምደው ባሕሩን ተሸግረው የክፋትን ሠራዊት ሁሉ ወደ ኋላ ጥለው በምድር ርስት እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርገው በኢየሩሳሌም እንደዘመሩ ሁሉ እኛም በዐቢይ ጾም የተጓዝነውን የተጋድሎ ጉዞ ማጠናቀቅ ያለብን ‹‹በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ፡፡… ››(ዘጸ. ፲፭፥፩) እንደተባለው እየዘመርን እናከብራለን እንጂ ወደዘፈን መመለስ የለብንም፡፡ ‹‹በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም፡፡›› (፩ኛ ቆሮ. ፭፥፰) እንደተባለም በዓላችን መድመቅ ያለበት በጽድቅ አንጂ በኃጢአት ሥራዎች አይደለም፡፡

አንዳንድ ክረስቲያኖች የትንሣኤን ደስታ ተስፋ ማድርግም ማክበርም ያለባቸው ብዙ አንበላበታለን ብዙ እንጠጣበታለን ብዙ ኃጢአት አንሠራበታለን ብለው ያቀዱ ያስመስልባቸዋል፡፡ ማሰብ የሚገባን ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን ድል ነው በድል ውስጥ ታላቅ ደስታ አለ፡፡ የሞትን የመውጊውን ብርት ሰብሯል፤ የሲኦል የሞት ሥልጣን ተሽረዋል፡፡ ነፍሳት ከሲኦል ነጻ ወትተዋል፣ ክርስቲኖች የጌታቸውን የደሙን ማህትም ይዘው ወደገነት የመግባት ጸጋ የተላበሱበት መሆኑን በማሰብ ነው፡፡

የጨለማው አገዛዝ ተወገደ ብለን በታላቅ ደስታ ነጭ ለብሰን ለማክብር፣ የልቅሷችን የትካዜችን የሰቆቃችን ጊዜ አበቃ ብለን በእልልታ ፣ የሕይወት ውሃ የሕይወት ምግብ ተጠምታ የነበረች ነፍሳችንን የሕይወት ማዕድ ተሳታፊ ለመሆን መብቃቷን በማሰብ ለሥጋ ወደሙ ለመቀበል በመትጋት፣ ሰው ከእግዚአብሔር፣ ሰው ከመላእክት፣ ሰው ከሰው ታራርቆ የነበረበት ጥላቻ የመለያየት ዘመን ማብቃቱን ሊመሰክር በሚያስችል መሰብሰብና መንፈሳዊ ሰላምታ በመለዋወጥ ሊሆን ገባል፡፡

ስለዚህ ከከንቱ ሕይወትና ከግብዝነት ርቀን በዓሉን ማክብር ገባል፡፡ በተለይ በአሁን ጊዜ በሀገራችን የሚታው ፍቅርና ሰላም መጥፋት ከበዓላችን ጋር አብሮ አይሔድም፡፡ በጾሙም ጊዜ በሀሜት፣ በጥላቻ በዘረኝነት፣ በስርቆት፣ሌላውን በማስጨነቅ፣ በመጨካከን አንዳንዶች ያሳዩትን ትዝብት ላይ የሚጥል ዝንባሌና ተግባር በማረም መሆን አለበት፡፡ እነዚህ የጠቀስናቸው ሁሉ የሰይጣን ሥራና ሐሳብ ናቸው፡፡

የእኛ በዓል ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠን በዓል ታላቅ መንፈሳዊ ጸጋ ነው፡፡ ኃጢአት አይስማማውም፡፡ ሁሉን በመውደድ፣ በመተዛዘን፣ በጽድቅ ሥራ ሁሉ ልናከብረው ይገባል፡፡ በጊዜያት ሁሉ ፍጹም ራሳችንን ልንገዛ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እያሰብን ከምልካም ሥራ ሳንለይ መኖር ይገባናል፡፡ በበዓሉ የምናስበው ጌታችንን ነው፤ የጌታችን ትእዛዘዝ ነው ሐዋርያውም ‹‹ ከሙታን የተነሣውን፥ ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፤›› እንዳለው ትንሣኤውን ነው፡፡ በዚህም አንጽና አንላላን፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡*

# ምሥጢር መጠበቅ ይሳነኛል

***ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! እንደምን ሰነበታችሁ? ስሜ ወልደ ገብርኤል ይባላል፡፡ የ፵ ዓመት ጎልማሳ ስሆን የቤተሰብ አስተዳዳሪም ነኝ፡፡ እነሆ ዛሬ የተቸገርኩበትን ነገር ላካፍላችሁ ወደድኩ፡፡ ጉዳዩ ብዙ ጊዜ ራሴን የታዘብኩበት ጉዳይ ነው፡፡ ሰዎች ለሌላ አትናገር፣ አንተ ብቻ እወቀው፣ ምሥጢር ነው ብለው የሚነግረሩኝን ነገር በውስጤ ለማቆየት እጨገራለሁ፡፡ በዚህም ምክንያት ከአንዳንድ ጓደኞቼ ጋር ግጭት ውስጥ አስገብቶኛል፡፡ ምሥጢር የሚባለውን ነገር ለሌላውም ሰው ምሥጢር ነው ብዬ የመንገር ልማድ አለብኝ፤ የነገርኳቸው ሰዎች ግን ታማኝ ሆነው ያልኳቸውን አይጠብቁም፡፡ ከዚህ የተነሣ ሰዎች ሁሉ እንደ እኔ እየመሰሉኝ እቸገራለሁ፡፡ ነገሩ ጥሩ አለመሆኑን ውስጤ እየነገረኝም እቸገራለሁ፡፡ ምን ትመክሩኛላችሁ፡፡***

ውድ ጠያቂያችን ስለምሥጢር ጠባቂነት ከማውሳታችን በፊት ምስጢር ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን በውል ማጤን አለብን፡፡ ምሥጢር ‹‹ አመሥጠረ›› አራቀቀ ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ረቂቅ የማይታይ፣ኅቡዕ፣ ሽሽግ ማለት ነው፡፡ ምሥጢር ለተወሰነ ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች ብቻ ተጠብቆ የሚቆይ ጉዳይ ነው፡፡  አንድም ምሥጢር በመንፈሳዊ ትርጉሙ የሰው ልጅ በራሱ ጥበብ መርምሮ ሊደርስበትና ሊያውቀው የማይችል አምላካዊ ግብር መንፈሳዊ ረቂቅ የማይታይ የሚደንቅ ማለት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ምሥጢርን ‹‹ በሰዎች ምርመራ ሳይሆን በእግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜም በሰው ሊገለጥ የሚችል፡፡ ለሰዎች ያልተገለጠ በእግዚአብሔር ዘንድ ታውቆ ያለ ምሥጢር ይባላል (ዘዳ፳፱፥፳፱)›› በማለት ይፈታዋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ምስጢርን ምን ብሎ እንደሚተረጉመው ከዐውዱ መረዳት ይቻላል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር ማለት ድንቅ ነገር ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን፡፡›› ሲል አስገራሚ፣ ታላቅ፣ አስደናቂ ነገር እነግራችኋለሁ ማለቱ ነው፡፡ (፩ኛ.ቆሮ ፲፭፥ ፶፩)፡፡ ለመረዳት ከሰው አቅም በላይ የሆነ ነገር እንደማለትም ነው፡፡ ‹‹ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም፡፡›› እንዳለ፡፡ (ማቴ. ፲፫ ፥፲፩)፡፡ የተሰወረ፣ ለመፍታት የሚያስቸግር ራዕይ፣ ሕልም ሁሉ ምሥጢር ይባላል፡፡ ነቢያት ሐዋርያት፣ ደጋግ ቅዱሳን ሁሉ ምሥጢርን የማወቅ ማለትም የተሰወረውን የማወቅ፣ ማንኛውም ሰው መረዳት የማቻለውን የመረዳት ጸጋ ባለቤት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ዮሴፍ፣ ዳንኤል እና ሌሎችም ብዙ ነቢያት ‹‹ ምሥጢርም ሁሉ ከአንተ የተሸሸገ አይደለም፡፡››  (ሕዝ. ፳፰፥፫) ይላል፡፡

በሌላም በኩል መጽሐፍ ቅዱስ ምስጢር በተገኘበት የማይነገር /የማይወራ/ ሲሆን ምስጢር እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በሚፈለገው ደረጃ ምሥጢርን የማይዝ ሰውም በመጽሐፍ ቅዱስ ሲዘለፍ እናስተውላለን፡፡ ጠቢቡ ‹‹ዘዋሪ ሐሜተኛ ምሥጢርን ይገልጣል፤ ከንፈሩን የሚያሞጠሙጥ ሰውን አትገናኘው፡፡›› በማለት የሚገስጸው እንዲህ በልብ የሚያዝን ነገር አውርቼ ካላደርኩ ብሎ የሚጨነቅን ሰው ነው፡፡ (ምሳ. ፳፥ ፲፱)

ውድ ጠያቂያችን እርስዎም የተቸገሩበት አጉል አመል ከዚህ መጨረሻ ላይ ጠቢቡ ከገሰጸው አመል ጋር የተዛመደውን ነው፡፡  አንድ ነገር ምሥጢር የሚሆነው ወይም የሚባለው ምን ሲሆን ነው የሚለው ታዲያ ሰዎች አንድን ጉዳይ ምሥጢር ነው ብለው የሚናገሩበትን፣ የሚሰሙበትን፣ የሚቀበሉበትን፣ ለመጠበቅ የሚጨነቁበትን ሁኔታና ደረጃ ይወስናል፡፡ አንድ ነገር ምስጢር ነው የሚባለው የሚገለጽበት ጊዜ ገና ከመሆኑ የተነሣ  ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም ተናጋሪው ወይም የሚነገርለትን ሰው አደጋ/ችግር/ፈተና ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ሆኖ ሲገኝ ሊሆን ይችላል፡፡

አንድ ነገር ምስጢር እንዲሆን ለምሥጢር ነጋሪው ሰው ለን ታማኝነትና ቁርጠኝነትም ይወሰናል፡፡ አንድ ሰው አትንገርብኝ›› ብሎ የነገረውን ነገር በመጠበቁ የወንድሙን ፍቅር በመጠበቅ ያለውን ታማኝነትና ፍቅር የሚገለጽበት ነገር ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችን ምናልባትም እርስዎ የባልንጀሮችዎን

‹‹ምሥጢር አልጠበቅሁም›› ብለው ሲናገሩ አትንገሩብን ተብለው የተቀበሉትን ምሥጢር ለጥቂት ወይም ለብዙ ሰው የመናገር ፈታኝ ዝንባሌና ተግባር አለብኝ ማለትዎ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ከዚህ አንጻር ስናየው በእርግጥም የሰዎችን ምስጢር ካለእነርሱ ፈቃድ የመግለጥ ድፍረት የወንድምን ፍቅር ስለሚያጎድል ጎጂ ነው፡፡ ምስጢርን አለመጠበቅ እርስዎ አስቀድመው በጥያቄው እንዳወሱልን ከባልንጀሮችዎ ጋር ያጋጫል፡፡ ከዚያም አልፎ አርስዎን ወይም ምሥጢሩ እንዲጠበቅለት የፈለገውን ሰው ሊጎዳ የሚችል መዘዝ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ጉዳት ሲባልም የሞራል፣ የሀብት የንብረት፣ የሕይወት ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ እርስዎ በዚህ ዝንባሌና ተግባር ከቀጠሉ ከጓደኞችዎ ጋር ብቻ በመጋጨት ፈተናዎ ላይወሰን ይችላል፡፡ ከባድ ቀውስና የብዙ ሰዎች ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ምናልባትም ሌላ የሥጋ ጉዳት ባያመጣ እንኳን መንፈሳዊ ሕይወትም ላይ ጉዳትም ያስከትላል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሰ በግልጽ ‹‹ክርክርህን ከባልንጀራህ ጋር ተከራከር፤ የሌላ ሰው ምሥጢር ግን አትግለጥ፡›› (ምሳ. ፳፭፥፱) ይላል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጊዜው ሳይደርስ ስለእርሱ መነገር የሌለበትን ነገር እንዳይናገሩ የሚያሳስባቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ‹‹ለማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው እነርሱ ግን ባዘዛቸውም መጠን ይልቅ እጅግ አወሩት፡፡›› (ማር. ፯ ፥ ፴፮) የሚል ቃል ተጽፎ እናነባለን፡፡ ዳግመኛም ሐዋርያቱን ጨምሮ በፍቅሩ ያቀረባቸውን ሰዎች ‹‹ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ፦ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን ለማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው፡፡›› (ማቴ. ፲፯፥፱) የሚል ቃል እናነባለን፡፡

ውድ ጠያቂያችን እርስዎ የገጠመዎት ዓይንት አመል ብዙዎች ዘንድ ሊኖር እንደሚችል በራስዎ ተሞክሮም አውቀውታል፡፡ በአባባልም ‹‹አትንገር ብሎ ቢነግረው፣ አትንገር ብሎ ነገረው…›› የሚባልባቸው ሰዎች አሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ዘንድ ደግሞ ምሥጢር በነገራቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን የያዙትን ምሥጢር ሳይገባቸው ሊያካፍሏቸው በሚጋብዟቸው ሰዎች ዘንድም ትዝብት ላይ መውደቅ ያስከትላል፡፡ ወሬኛና ነገር አባካኝ ያስብላል፡፡

ስለዚህ እርስዎም ከላይ አስቀድመን የጠቀስናቸውን ጉዳቶች በማሰብ ከዚህ መሰል ድርጊት መቆጠብ ይገባዎታል፡፡ ከዚህ አልፎ ደግሞ ምሥጢር ጠባቂነት የሚያገኘውን በጎ ዋጋ ማሰብም ተገቢ ነው፡፡ ምስጢር መጠበቅ ከመከራ ይሰውራል፡፡ የኢያሪኮዋ ረዓብ ሁለቱ የእስራኤል ሰዎች በስውር ለመሸሽግ የገባችውን ቃል አክብራ ምሥጢራቸውን ጠብቃ በመገኘቷ ከመከራ ድናለች፡፡ የእስራኤል ወገን ኢያሪኮን እየሰባበረ ሲገባ እርሷ ግን ተርፋለች፡፡

ጻድቁ ዮሴፍ ድንግል ማርያምን በእርሷ የሆነውን ነገር ባለመግለጥ ለመቆየት በመረጠ ጊዜ ጻድቅ ለመባል በቅቷል፡፡ ታላቅ ሰማያዊ ምሥጢርም የመሲሕ የማዳን ሥራም ተገልጦለታል፡፡ ድንግል ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ሰማዊውን ታላቅ ምሥጢር በልጇም የሚደረገውን ታለቅ ድንቅ ነገር ሁሉ የምታስተውልበትን ደረጃ ሲገልጽ ‹‹ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር፡፡›› (ሉቃ. ፪፥፲፱) ብሏል፡፡

ውድ ጠያቂያችን እርስዎ መሸከም የማይገባዎት አንዳንዶች ሐሜትንምሥጢር እንደሆነ ያስባሉ፡፡ ባልንጀራን ማብጠልጠል መክሰስን ምሥጢር ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶች በሌሎች ላይ ፈተና የሚያመጣ ሴራን ሁሉ ምሥጢር አድርገው ያስባሉ፡፡ ይህን የመሰለ ነገር ግን መፍረስ ያለበት፤ መወገዝ ያለበት ከንቱ ንግግር ነው፡፡ ለምሳሌ አይሁድ መቃብር ተባቂዎችን በሐሰት የፈበረኩትን ክንቱ ወሬ እንዲያወሩና የክርስቶስን የትንሣኤ ምሥጢር ግን እንዲሰውሩ እንዳይናገሩ መክረዋቸው ነበር፡፡ እንዲህ ዓይንቱ ክንቱ ምክር ግን የሚፈርስ ነው፡፡ እርስዎም እንዲህ ያሉ ርባና ቢስ ወሬዎችን ምሥጢር ብለው በመቀበል ለመሸክም እንዳይጨነቁ ማሳሰብ እንፈልጋለን፡፡

በአጠቃላይ ሲታየም ምሥጢር የሚባለው ጊዜው ባለመድረሱ፣ የሚያስከትለው ጉዳት ከመኖሩ፣ በመነገሩ በግለሰብ ወይም በሆነ ማኅብረሰብ ላይ ፈተና የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ምሥጢር ሆኖ በልብ ተሰውሮ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ ሰዎች የነገሩንን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ነገሮች የሚያከትሉትን ተፅዕኖ ከግምት አስገብቶ በስወር መተው ያለበትን ነገር በመተው ብርቱ ውሳኔ ሊወስኑ ይገባል፡፡ ይህንን ሲያደርጉ ደግሞ ከሰይጣንና ከከንቱ ነፃ ይወጣሉ፡፡ ይህን ለማድረግ የነበረዎት ሊያስቸግርዎት ቢችልም በጸሎትና በስግደት ከንቱ አመልዎን ሊያስተካክሉ ይገባል እንላላን፡፡